***Journal of Afroasiatic Languages/Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL)***

Volume 11, Number 2, 2022

# CHANGES IN ETHIOPIA'S POLITICAL IDEOLOGY

## (በኢትዮጵያ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ለውጦች)

AYELE ADDIS AMBELU & ABEBE ZEGEYE

## Abstract

*Ideological discourse in Ethiopia began during the student movement of the 1960s. It was a time when most sections of Ethiopian society, including students engaged in an intense discussion of socialist ideas and beliefs. At the time, political ideology, class struggle, social rivalry, ethnic questioning, politics, and party politics were among the main topics discussed in Ethiopia.*

*A problem arises because external political ideologies do not reflect Ethiopian political, economic, and social conditions but are trying to be applied from a viewpoint that ignores local imperatives. Although the question of democracy arose as all the political forces of the day followed the philosophy of socialism, the main questions were about group rights, and equality between nations and religions.*

*The turmoil in Ethiopia over the past five decades is fueled by differences in worldview, political affiliation, class, ethnicity, and religion in a way that does not incorporate knowledge and experience of foreign implementations. Today, the view of the country is one of a country at a crossroads between alternative ways ahead.*

*Analyzing the country's realities to heal our fractures and creating an inclusive vision learned from international experience will be the bridge to Ethiopia's future. It is imperative that Ethiopians work together to ensure*

*sustainable development by overcoming obstacles erected between different domains.*

*Socialism, Liberalism, and other ideologies have been implemented elsewhere in the world with varying degrees of success, as have other political alternatives, such as revolutionary democracy. If we are to correct the flaws of the past, it is essential to balance competition and cooperation, balance competing ideologies and not be a prisoner of ideology alone.*

*This article aims to examine the nature, history, characteristics, strengths, and weaknesses of the systems and ideologies tested in Ethiopia.*

**Keywords**: Changes, Ethiopia, Ideology, Politics

# በኢትዮጵያ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ለውጦች


**አህፅሮት**

*በኢትዮጲያ በርዕዮተ ዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ንግግሮች የተጀመሩት በ1960ቹ በተቀጣጠለው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት ተማሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ የማህበረሰባችን ክፍሎች በከፍተኛ ሁኔታ በሶሻሊዝም ዕሳቢዎች እና እምነቶች ዙሪያ የተወያዩበት ወቅት ነበር። በዚያ ዘመን ነው፤ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ የመደብ ትግል፣ ማህበራዊ ውግንና፣ የብሄር ጥያቄ፣ ፖለቲካ እና የፓሪቲ ፖለቲካ በኢትዮጲያ የመለያያ አርዕስት ነበሩ። በወቅቱም ብዙ ክርክሮች ሲደረጉ የነበረ ሲሆን ከዛም ባለፈ በጎራ በመከፋፈል የከፋ እልቂት እንዲፈጠር መንገድ ከፍተዋል። ለዚህም ችግር እንደምክንያት የሚጠቀሰው ርዕዮተ ዓለሞችን ከኢትዮጲያዊ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታዎች የመነጩ ሳይሆን ከውጭ የተቀዱ እንደወረደ ተግባራዊ ለማድረግ የሚሞከሩ መሆናች ነው። ሁሉም በሚያስብል ሁኔታ በጊዜው የነበሩት የፖለቲካ ሀይሎች የሶሻሊዝም ፍልስፍናን የሚከተሉ በመሆናቸው የዴሞክራሲ ጥያቄ ቢነሳም ዋናዎቹ ጥያቄዎች በቡድን መብት ዙሪያ የታጠሩ እና በዋናነትም በብሄሮች ና በሀይማኖቶች መካከል እኩልነት እንዲመጣ በመጠየቅ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። ባለፉት አምስት አስርት አመታት ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ትርምስ ከውጭ የተገኘውን ዕውቀት ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ባላገናዘበ መንገድ በርዕዩት አለም ልዩነት፣ በፖለቲካ አሰላለፍ፣ በመደብ፣ በጎሳ እና በሃይማኖት መከፋፈል የተፈጠረ ችግር ነው። ዛሬም በሀገሪቱ ያለው እይታ ሙሉነት የጎደለው አንዱን አዝሎ ከፊሉን አንጠልጥሎ ጉዞ ነው። ስብራቶቻችን ለማከም ሀገራዊ ነባራዊ እውነትን ተንትኖ ከአለም አቀፍ ተመክሮ የተማረ አካታች እይታ ማበጀት ለኢትዮጵያ መውጫ መንገድ መሻገሪያ ድልድይ ይሆናታል። በተለያዩ ጎራዎች መካከል የሚስተዋልን ዋልታ ረገጥነት በመተው የተለያዩ ፍላጎቶችን በማስተናገድ ፍክክርና ትብብርን ሚዛን አስጠብቆ በማስኬድ፣ ለርዕዮተ ዓለሞች ብቻ ተገዢ እና እስረኛ ባለመሆን፣ ከቀደመው ወረቶቻችን ሰንቆ ጉድለቶችን በማረም ሁለንተናዊ እድገት ለማረገገጥ መስራት የግድ ይላል። በዓለማችን እንደ ሶሻሊዝም፤ ሊበራሊዝም እና ሌሎችም ርዮተ-ዓለሞች ተግባራዊ ሆነዋል። በተመሳሳይ መልኩ በሊብራሊዝም ዘውግ ውስጥ የሚመደቡ እንደ ቀደምት ሊብራሊዝም እና ኒዮ-ሊብራሊዝም፤ "ሦስተኛው መንገድ" ተብሎ የሚታወቀው እና በሊብራሊዝም እና በሶሻሊዝም ላይ የሚነሱ ትችቶችን ለማረም ጥረት የሚያደርገው ሶሻል ዴሞክራሲ፤ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ጥረት የሚያደርገው ልማታዊ መንግሥት፤ እንዲሁም እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ያሉ እና ሌሎችም የፖለቲካ አማራጮችና ኘሮግራሞች ተግባራዊ ሆነዋል። የዚህ ፅሁፍ ዓላማም በኢትዮጲያ ውስጥ የተሞከሩትን ስርዓቶች እና ርዕዮተ አለሞች ምንነት፣ ታሪክ፣ ባህሪያት፣ ጠንካራ ጎን እና ህፀፆቹን መመልከት ነው።*

***መግቢያ***

*የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በኢትዮጵያ የለውጡ ሥርዓት እና ርዕዮተ-ዓለም ምንነት፣ ታሪክ፣ ባሕሪያት፣ ጠንካራ ጎንና ህፀፅን ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ለውጦች ከ1950ዎቹ ወዲህ ምን እንደሚመስል መዳሰስ ነው። አሜሪካዊ ሶሺዮሎጂስት ሴይመር ማርቲን ሊፕሴት (1994፣ ገፅ፣1-22) 'የዲሞክራሲ ማህበራዊ ፍላጎቶች" በተሰኘ ጽሑፉ የሚከተለውን ትንታኔ ይሰጣል፤ "በተወሳሰበ ሕብረተሰብ ውስጥ ዴሞክራሲ ሲተረጎም የአስተዳደሩን ሹማምንት ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ሕገ መንግሥታዊ ዕድሎችን የሚሰጥ የፖለቲካ ሥርዓት ከሕዝቡ ብዛት ያለው ክፍል የፖለቲካን ሥልጣን ለመያዝ ከሚወዳደሩት መካከል በመምረጥ ታላላቅ ውሳኔዎችን እንዲተላለፉ ለማድረግ የሚያስችል መሣሪያ ነው።"*

*በሀገራችን ለዴሞክራሲ መንገድ የሚጠርግ ጠንካራ የመንግሥት ቢሮክራሲ መገንባት፣ ብቁ፣ ተወዳዳሪና የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፣ በተመረጡ ዘርፎች ላይ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን በመፍቀድ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ባለፉት 27 ዓመታት ተግባራዊ ለማድረግ የተሞከረውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ልማታዊ መንግሥት ርዕዮተ-ዓለም፣ መሠረታዊ እሳቤና የሚነሱ ዋና ዋና ትችቶችን እንመለከታለን። ከኢህአዴግ ውስጣዊ ለውጥ ጋር ተያይዞ በዶ/ር ዐቢይ አህመድ የሚመራው የብልጽግና ፓርቲን የመደመር እሳቤ ከፕራግማቲዝም ምንነት በመነሳት በመደመር ፍልስፍና መካከል ያለውን ገፅታ ይቃኛል።*

*ባለፉት ሃምሳ ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል በመለዋወጥ ላይ ይገኛል። በየጊዜው ለሚስተዋለው ለውጥ በርካታ ታሪካዊ መንሥኤዎች አሉት። ከ1950ዎች ወዲህ በተከታታይ ቀጣይነት ባለው ሁናቴ በመካሄድ ላይ ያሉት ግራ ዘመም አብዮቶችና መሰል ፖለቲካዊ ለውጦች በዋናነት ይጠቀሳሉ (አለም፣ 1990)። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በየዘመኑ የታዩት የፖለቲካ ባሕል ለውጦች ሁሉንም ዘርፎች የሚያካትቱ ባይሆኑም በቅርብ ጊዜ ከኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተወሰኑ የፖለቲካ ባሕሎች ቀስ በቀስ የተለወጡባቸው አራት ዋና ዋና ምዕራፎች አሉት። እነሱም ከ1933 ከፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ በኋላ እስከ 1940ዎቹ መገባደጃ፤ ከ1950 ዓ.ም-1980 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት፣ ከ1980ዎች እስከ 2008 ዓ.ም እና ከ2008 ዓ.ም ወዲህ ናቸው።*

## የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል እስከ 1950ዎቹ ድረስ

*የኢትዮጵያ ከፊል ዘመናዊ ሀገረ-መንግሥት ከተመሰረተበት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ አንስቶ እስከ የተማሪዎች ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ፍትሕ ጥያቄዎች ትግል መቀስቀስ ማለትም 1950ዎቹ ድረስ አዝጋሚ ለውጦች ተካሂደውበታል። ዜጎችና የተለያየ ማሕበራዊ መሠረት የነበራቸው ልሂቃን ስለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት፤ መንግሥታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በሥርዓቱ ውስጥ ስላላቸው ሥፍራና ተሳትፎ ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜ በሀገሪቱ በፖለቲካ ሥርዓቱ ላይ የበላይነት የተጎናጸፉ ልሂቃን በሚያራምዱት የዘመኑ ትርክት የሚመራ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል (Lemma, 1979)።*

በማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ በፖለቲካው መስክ ጉልህ እንቅስቃሴ ያደርጉ የነበሩት ውስን ልሂቃንና ዜጎች ስለሀገራቸው የነበራቸው ዕውቀትና አረዳድ በአብዛኛው መለኮታዊ በሆነው የአገዛዝ እሳቤ ነበር (Crummey, 1990)። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ በሙሉ የፖለቲካ ሥልጣን ሃይማኖታዊ መሰረት ስለነበረው ነው። በዚሁ አረዳድ እስከ 1923 ዓ.ም የሀገሪቱ የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት መረቀቅ ድረስ መተዳደሪያ ተደርጎ ይታይ በነበረው የክብረ ነገሥት ትርክት ላይ ተመርኩዞ ነበር (CAULK, 1972)። ክብረ ነገሥትን በዘመኑ የሚቀበለው አብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የፖለቲካ ሥርዓት፣ የነገሥታቱን እና ሌሎች ተያያዥ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ከሥልጣን ምንጭነት አኳያ የራሱ የሆነ ዕውቀት፤ ስሜትና ድምዳሜ ይዞ መቆየቱ አያከራክርም። ስለ ሀገሪቱ፣ ስለ ንጉሡ ነገሥታዊ መንግሥት ሥርዓት፣ ስለመሪዎች እና ስለዜጎች ተሳትፎ ውስንነት፤ ስሜትና ድምዳሜዎቹም ከተጨባጭ ምክንያታዊነት ይልቅ በሃይማኖታዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነበር። በእርግጥ ይህ ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜም በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በሁሉም ልሂቃንና የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ተመሳሳይ አልነበረም (Lewis & Jewell, 1976)። በአጠቃላይ በሥርወ መንግሥቱ የፖለቲካና የሃይማኖት ማንነት የታጠረ የከበርቴ ልሂቃን ንዑስ ባሕል ነበር። በመሆኑም በተከታታይ በታዩት የፖለቲካ አብዮቶችና ለውጦች ሁሉም የመሰረቱትና ያዳበሩት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ባሕል ነበር ለማለት ያስቸግራል።

በተለያዩ የፖለቲካና ማሕበራዊነት ተራምዶት ውስጥ ያለፉ ልዩ ልዩ ኃይሎች ለዘመናት የበላይነት ተቆንጥጦ የነበረውንና በክብረ ነገሥት ትርክት ላይ የተመሠረተውን የፖለቲካ ዘይቤ የሚቃረንና የሚቀናቀን አዲስ የፖለቲካ ባሕል ብቅ ማለት ጀምረውም ነበሩ። ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር ከ1950ዎቹ በፊት በኢትዮጵያ ከመንግሥታዊ ሃይማኖት ውጭ የሌሎች ሃይማኖቶች እምነት ተከታይ ልሂቃንን እምብዛም አላስተናገደም የሚል ትችት ይጠቀሳል። በሌላ በኩል ስለ ሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት እና እንደዜጋ በማናቸውም ፖለቲካ ሥርዓቱ በሚፈቅደው ውሳኔ የነበራቸው ንቁ ተሳትፎ ውስን መሆኑ ይገለጻል። ነገርግን በሃገሪቱ የነበሩ የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና በቤተመንግስት የነበራቸውን ሚና ያላገነዘበ ነው።

በንጉሣዊው አገዛዝ ዘመን *"ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ"* ከሚለው ብኂል መረዳት የሚቻለው የሕዝብ መለኮታዊ ተገዢነት መሆኑን ሲሆን ቀስ በቀስ ሀሳቡ እየተሸረሸረ ያልተማረውም ሆነ የተማረው ወገን የአመፅ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ማካሄድ ችሏል (Borruso, 2013)። በነገስታቱ ላይም ከንጉስ አምደጽዬን እስከ ቀደማዊ ሃይለስላሴ ድረስ ዙፋናቸውን የነቀነቃ ህዝባዊ አመፅ እንዳጋጠማቸው ይታወቃል።

የመንግሥት ሃይማኖት በፖለቲካ ውስጥ በቀጥታ ተሳትፎና ወሳኝ ሚና ነበረው (Markakis, 1989)። ለአብነት፡-ንጉሥ ተቀብቶ የሚነግሠው በሃይማኖት መሪዎች በሚካሄደው የንግሥና ሥነ ሥርዓት አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። በዚህም ከተለመደው አሰራር ውጭ ለአመራር ይበቁ የነበሩ የፖለቲካ ሰዎች ዕድል ሳያገኙ ሀገራቸውን ሳይጠቅሙ አልፈዋል። በሃይማኖት መሪዎች ቅስቀሳና ተቃርኖም የተነሳ አንዳንድ መሪዎች እንዳለመታደል ህልማቸው ከንቱ ሆኖ አልፈዋል። በኢትዮጵያ የረጅም መናት ታሪክ የሀገር

መሪ በሰላም የሚቀየርበት አጋጣሚ አጅግ ብርቅ ነበር። በተለይም የሰለሞናዊ አገዛዝ ርዕዮተ-ዓለም የሀገሪቱን የፖለቲካ ባሕል ለአያሌ ዓመታት ሲዘውር ቆይቷል። ይህም መንግሥት በሕዝብ ፍላጎትና ነጻነት የማይቀየር መለኮታዊ በመሆኑ *"ስዩመ-እግዚአብሔር"* ተደርጎ ይታያል (Pankhurst, 1997)። በብዙሃን ዘንድ መንግሥት ለመቀየር ብቸኛው መንገድ በሕዝባዊ አመጽና በአብዮት ተደርጎ እንዲታይ አድርጓል። በዚህም በፖለቲካ ባሕሉ ውስጥ ሕዝባዊ አመጽ ጉልኅ ሥፍራ እየያዘ ሊመጣ ችሏል።

## የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ከ1950ዎች እስከ 1980ዎቹ

ከዘመናዊ ትምህርትና ከሌሎች አዳዲስ ተቋማት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከ1950ዎቹ ወዲህ በተማሩ ዜጎች ዘንድ ስለ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓትና የመሪዎች ሀገራዊ ውሳኔ አሰጣጥና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ስለነበረው የዜጎች ተሳትፎ የነበረው አረዳድ መቀየር ሲጀምር የፖለቲካ ባሕሉም በዚያው ልክ ቀስ በቀስ እየተለዋወጠ መጥቷል (Harbeson, 1977)። በመሆኑም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባሕል መሠረቱ ሊለወጥ የቻለው የዘመናዊ ተቋማት ትሩፋት ማለትም ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችና የመገናኛ ብዙሃን መስፋፋትን ተከትሎ ነበር። እነዚህ ተቋማት በዘመኑ ዋነኞቹ የፖለቲካና ማህበራዊነት ለውጥ ሐዋሪት ሲሆኑ በፖለቲካ ባሕል ለውጥ ምዕራፍ ውስጥ በክብረ ነገሥት ተረክ ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት ታሪክ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጥያቄዎች ሊያነሱበት ችለዋል። ቀስ በቀስም የነገሥታት የፖለቲካ ሥርዓት ቅቡልነት ተሞገተ፣ ዜጎችም በሀገራዊ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የራሳቸውን የተሳትፎ ሚና በተመለከተ ዳር ተመልካች መሆንን እየተው መጡ። ቁጥራቸው በቀላሉ የማይገመት ዜጎች ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥርዓት፣ ስለ ሀገራዊ አንድነት ጉዳዮች፣ ስለ ውሳኔ አሠጣጥና ስለ ዜጎች ፖለቲካዊና ሰብዓዊ መብቶች ዕውቀት፤ ስሜትና ድምዳሜ ላይ ደረሱ። በመጨረሻም በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ግንባር ቀደም መሪነት የአዲሱ ትውልድ አዲስ የፖለቲካ ባሕል መምጫ ጉዞ ተጀመረ (Lemma, 1979)።

አዲሱ የፖለቲካ ባሕል ለ1966ቱ ሕዝባዊ አብዮት ርዕዮተ-ዓለማዊ ደጀን ሆኖ ከአብዮቱ ማግሥት በስኬትና በውድቀት ወደ ሌላ ውስብስብ ምዕራፍ ተሸጋገረ። አዲሱ ፖለቲካዊ ባሕል ስኬት ዜጎች በተለይ ስለ ዘውዳዊ ሥርዓትና የመሪዎቹ መለኮታዊ ቅቡልነት ላይ ተመርኩዞ ለ ዘመናት ተቀባይነት የነበረው ትርክት በአዲስ አስተሳሰብ መቃኘት ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ውድቀቱ በሀገራዊ ጉዳዮች ውሳኔ አሠጣጥ ላይ የዜጎች ሥፍራና ተሳትፎን በተመለከተ የነበረው ግንዛቤ፣ ውስጣዊ ስሜትና ድምዳሜ የወታደራዊው መንግሥት የሽብርና የአፈና እርምጃ ውጤት መሆኑ አልቀረም (Gebeyehu, 2010)። ከደርጉ መንግሥት የጸረ-አብዮተኛ ፍረጃ እርምጃ መፋፋም ምክንያት በበርካታ ዜጎች ዘንድ እጅግ ፍርሃት መንገስና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባሕል መገለጫ እየሆነ የመጣው "ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ" የሚል ሆኗል።

የፖለቲካ ታሪክ ተንታኝ ምሑራን "በወንድማማቾቹ በመንግሥቱ ንዋይና ግርማሜ ንዋይ የተመራው መፈንቅለ መንግሥት የዴሞክራሲ ሥርዓት ለውጥ ባሕል ባለመኖሩ በሀገሪቷ ታሪክ የአመጽ መንገድን ያስቀጠለ ነበር" ሲሉ ይከራከራሉ (Kebede, 2015)።

በዚህ ዐይን ገላጭነት *"መሬት ላራሹ እና የብሔር ጥያቄን"* ያነገበው የተማሪዎች እንቅስቃሴም ያው የአመጽ አካሄድን የተከተለ ነበር (Gebeyehu, 2010)። የተማሪዎቹን ጩኸት ቀምቶ ወደ ስልጣን የመጣው ወታደራዊው ደርግ ጁንታም በአብዮት ስም የአመጸኞች ቡድን ስብስብ ነበር። የደርግ መንግሥት ከእርስ በርስ ጦርነት በኋላ የተወገደውም በተለመደው ሕዝባዊ አመጽ ነው። በትጥቅ ትግል ሥልጣን የተቆናጠጠው ቡድን በተማሪዎች የአመጽ እንቅስቃሴ የቀሰመውን የፖለቲካ ባሕል ለመቀየር እንደተሳነው ዛሬም የሚታይ ሀቅ ነው። ቡድናዊነት፣ ዘረኝነት፣ ፍረጃ፣ ጥላቻ፣ ኢ-ሰብአዊነት፣ አመጽ፣ ማሳደድ፣ ማሰር፣ ማሰቃየትና መግደል፣...ወዘተርፈ አስከፊ ድርጊት መለያዎች የፖለቲካ ባሕል ሆኖ ለዘመናት ተሸጋግሯል።

ታዋቂው የሥነ ጽሑፍ ሰው ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን *"አፋዊ ሆንን...ቤታችንስ አንድ ነው!"* በተሰኘው የግጥም ሥራው ስለአዲሱ ትውልድ በእጅጉ ተጨንቋል። እንድምታው ትውልዱ አፋዊ እንጂ እደቀደምት አባቶቻችን ልባምነትን አልወረሰም የሚል ቁጭት አዘል ሀሳብ ያንሸራሽራል። ትውልዱ ከበጎ ነጻነትና ልባዊ በረከት ይልቅ ከንቱ ሽንገላን ነው ያነገበው ይላል። ጸጋዬ ጠለቅ ባለ ስሜት ሲገልጽ በውስጣችን ተከፋፍለን እንዲያው ለይስሙላ በለበጣ የምንኖር ከፍቅር ይልቅ ቅራኔን በልባችን የምናኖር ሆነናል። ሰብዓዊነት እርቃኑን እየቀረ መጥፎ ጥላቻ፣ ቂም በቀልና አልጠግብ ባይነት ነግሶብናል ሲል በምሬት ይገልጻል። አሁን ያለው ትውልድ መጠየቅና መመራመር ሲጀምር ትውልዱ የበራለትን ግንዛቤ ከእኛን እውነታ ጋር በማላተም እንደፍቅበታለን። በዚህም ውስጣዊ መራራቅ የመፈጠሩን ጉዳይ አጽንዖት ሰጥቶ ተምሳሌት በሆነች እንኮዬ በሚላት ባልቴት የእሷ ድንቁርና በእጅጉ ተሸሎ ማየቱን ያጋራናል። ሀገራዊ ሕብር ማንነታችን በአጓጉል የፖለቲካ ዘይቤ ምክንያት ሊያቀራርበን ሲገባ ሆድና ጀርባ እንዳደረገን በጥሩ ሁኔታ ይነግረናል። በትውልዱ የዘራነውን እንድናጭድ ግድ የማይሰጠን ለልጆቻችን ከሚዛናዊ ሀቅ ይልቅ የፍርሃት ድባብን የምናወርስ ሲል በሰቀቀን ሀሳቡን አስፍሮታል። ከረጅም ግጥሙ በድምጽ ተቀርጾ ካገኘነው በአጭር ስንኝ ቀንጭበን ስንወስድ፣

ቤት ብለን ለልጆቻችን ያወረስናቸው፤
ፍቅር የሞተበት ቤታችን አንዱ ነው።
አባቶቻችን ልባም እኛ አፋም፤
እሳት አመድ ወለደ ሆነን እንጂ፤
ቤታችንስ አንድ ነው።
ነጻነት ብለን ባርነት፤
ሕይወት ብለን ሞት ለልጆቻችን አወረስን።

የሀገራችን ፖለቲካ እንደማናቸውም ባሕል የፖለቲካ ሥርዓት ሲለወጥ በሦስቱም ዘርፎች ሙሉ ለሙሉ ከመቀየር ይልቅ የተወሰነ ዘርፍ በነበረበት ይቀጥላል ወይም ወደባሰ አዙሪት ይደርሳል የሚል ነው ሲሉ ብዙዎች ይተቻሉ። ዜጎች ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ማንነት፣ የፖለቲካ ሥርዓት፤ መሪዎችና ሌሎች ጉዳዮች ልሂቃን የነበራቸው ዕውቀት፤

ስሜትና ድምዳሜ ከ1966ቱ አብዮት መፈንዳት በኋላ ተለውጧል። ይሁን እንጂ የፖለቲካ ባሕል ለውጡ ያልተሟላና የራሱ ተግዳሮቶች የነበሩበት ነው። የዜጎች በፖለቲካ ሥርዓቱ በነጻነት ያላቸው ተሳትፎ መገደቡ አዲሱ የፖለቲካ ባሕል ከአብዮት በፊት በከፋ ሁኔታ በሽብርና በአፈና ምክንያት የራሱን ቅርጽና ጠባይ ይዞ ቀጥሏል። ይህ ሁኔታ እስከ 1980ዎቹ የመንግሥት ለውጥና ከዚያም በኋላ ባሉት ጊዜያትም መዝለቁ ይስተዋላል።

በኢትየጵያ የፖለቲካ ሥርዓት በርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ውይይቶች ብቅ ማለት የጀመሩት በ1960ቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ነበር (Crewett & Korf, 2008)። በዚህ ወቅት ተማሪዎችን ብቻም ሳይሆኑ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችም በሶሻሊዝም ፋሽን ዝንባሌ ተጽዕኖ ሥር ወደቁ።

በዚያን ጊዜ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ባላገናዘበና ለነበረው ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግርም መፍትሄ የማያመጣ ጉንጭ አልፋ ክርክሮች ሲደረጉ የቆየ ሲሆን ከዚያም አልፎ ተርፎ ጎራ የለየ የእርስ በርስ እልቂት እንዲፈጠር በር ከፍቷል (Harbeson, 1977)። ለችግሩ እንደምክንያት የሚጠቀሰው የ(ሶሻሊዝምን-ኮሚኒዝምን) ርዕዮተ-ዓለምን ከሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ እውነታዎች ጋር በልክ ሰፍቶና አጣጥሞ ከመሄድ ይልቅ፣ ኢትዮጲያዊ መልክ ሳይኖረው የውጭን ፍለስፍና እና አሰራር ከማስረፅ ጅምሮ እስከመተግበር ድረስ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ተግባራዊ አሰራር ለመፈፀም መሞከሩ ነው (Abbink, 1993)። አብዛኛውን ስራ ከመፈፀም እንደገና መጀመር ከምስራቁ እና ከምዕረቡ በመቅዳት ፤ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ ለመሞከር መባዘኖች ታይተዋል። በጊዜው የነበሩት የፖለቲካ ኃይሎች ግራ ዘመም የሶሻሊዝም መርህን ተከታይ በመሆናቸው የዴሞክራሲ ጥያቄ ቢነሳም አብዛኞቹ ጥያቄዎች በቡድን መብት ዙሪያ የሚያቀነቅኑ ሲሆን በዋናነትም በብሄሮችና በሃይማኖቶች መካከል የእኩልነት ጥያቄ ላይ ያተኮሩ ነበሩ።

በሶሻሊዝም ሆነ በሊብራል አስተሳሰብ ዙሪያ የታየው አቋም የሀገሪቱን ነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ከመረዳት አንፃር ጠቃሚውን በአግባቡ መለየትና መምረጥ ላይ ሳይሆን ከውጭ የመጣውን ንድፈ ሀሳብ ትንታኔ የልርታ ልርታ ፉክክር የታጠረ መሆኑ ችግሩን ሊያባብሰው ችሏል (Tareke, 2002)። በሁሉም ጉዳይ ሰክኖ መነጋርና መደማመጥ የሚቻልበት ችግር ፈቺ አካሄድ ስለመነመነ በእንሞክርበት አጓጉል ዘይቤ ፖለቲካችን ቅጥ አልባ ሆነ። የፖለቲካ ስልቶቻችን እንዲያው ከውጭ የተቀዱን እንደወረደ ተግባራዊ ለማድረግ ቀርቶ በአግባቡ ተጠንቶ ለሚሞከሩትም በጥንቃቄ መርምሮ የማረምና ውጤታቸውን መዝኖ የመተግበር ልምድ አልነበረም።

በኢትዮጵያ የምዕራቡ ዓለም ዘመናዊ ፍልስፍና ብቅ ማለት የጀመረው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲሆን 1960ዎቹም የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም፣ የመደብ ትግል፣ ማሕበራዊ ውግንና፣ የብሄር ጥያቄ፣ የሰለጠነ የፓርቲ ፖለቲካ የተጋጋመበት ወቅት ነበር (Sarah፣ 2003)።

ባለፉት መቶ ዓመታት በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረው የፖለቲካ ትርምስ ችግር ከውጭ የተገኘውን አዲስ ልምድ ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ባላገናዘበ አኳኋን ለመተግበር መሞከሩ ነው።

**የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ከ1980ዎቹ እስከ 2008 ዓ.ም**

በ1980ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ወደ ሶሻሊዝም ምዕራፍ ተሸጋገረ። ይኸውም በ1950ዎቹ የታህሳሱ ግርግር ወይም ጸሃረ-መንግሥት የተለያዩ ልሂቃንና ዜጎች ግንዘቤ፣ ስሜትና ድምዳሜ መቀየር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

በየካቲት1966 ሕዝባዊ አብዮት በላቀ ሁኔታ ከጥቂቶችና ሃይማኖታዊ መሠረት ከነበራቸው ባሻገር ሰፊ ማሕበራዊ መሠረት የነበራቸው ልሂቃንና ዜጎች ስለ ሀገራቸው ፖለቲካ ሥርዓትና መዋቅር፣ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትና ስለወደፊቱ አካሄድ ያላቸው ግንዛቤና ድምዳሜ እየተለወጠ መጥቷል። የአገሪቱን ታሪክና የፖለቲካ መዋቅሩን በተመለከተ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የፖለቲካ ልሂቃንና ዜጎች ጭምር በአዲስ መልኩ የራሳቸውን ዕውቀት፤ ስሜትና ድምዳሜ ላይ ደረሱ። ሆኖም በዚያው ልክ ከነዚህ የፖለቲካ ልሂቃንና ዜጎች ፍጹም በተለየ መልኩ ሌሎች ኃይሎችም የሀገሪቱን ታሪክና ፖለቲካ አወቃቀር በተመለከተ ተጻራሪ ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜ ነበራቸው። መንግሥታዊ የበላይነት ከነበረው ባሻገር ብዙሃን ቋንቋና ማሕበራዊ መሠረት ባላቸው ልሂቃን አማካኝነት ካቆጠቆጠው የፖለቲካ ባሕል ጋር ተያይዞ አማራጭ የፖለቲካ ንዑስ ባሕል እየዳበረም መጣ (Paulos፣ 2007)።

በአጠቃላይ ከ1980ዎቹ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ የነበረው የፖለቲካ ባሕል ከዚህ የሚከተሉት ዋና ዋና መገለጫዎች ነበሩት። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤

- *የሀገሪቱን ታሪክ፤ የፖለቲካ መዋቅሩንና ሥርዓቱን በተመለከተ የነበረው የልሂቃንና የዜጎች ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜ ፈጽሞ ወጥነት አልነበረውም። የበላይነት ከነበረው መንግሥታዊ የፖለቲካ ባሕል በተጨማሪ በተለያዩ ኃይሎች፣ ልሂቃንና ዜጎች ዘንድ ተጨማሪ የፖለቲካ ንዑስ ባሕሎች ነበሩ። እነዚህ ንዑስ ባሕሎች ደግሞ ከመጣጣም ይልቅ እርስ በርስ የመጻረር ጠባይ ነበራቸው። ይህ የፖለቲካ ንዑስ ባሕሎች ተጻራሪነት የዜጎችን በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የነበራቸውን ፖለቲካዊ ተሳትፎ በእጅጉ ጎድቶታል።*
- *የፖለቲካ መዋቅሩን እና የሀገራዊ ጉዳዮች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ የነበረው ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜ በአንጻሩ በሰፊ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የነበረ ቢመስልም በእርግጥም በልሂቃን የተወሰነ ነበር።*
- ከ1980ዎቹ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ *በነበረው የፖለቲካ አካሄድ ዜጎች በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የነበራቸው ሥፍራና ተሳትፎ በተመለከተ የነበራቸው ዕውቀት፣ ስሜትና ድምዳሜ በፖለቲካ ልሂቃኑ አመለካከትና አቋም ተጽዕኖ ቁጥጥር ሥር የወደቀ ነበር። ይህ ሲባል ዜጎች በስማቸው የሚንቀሳቀሱ ልሂቃኖቻቸውን በመታገል ይህን የፖለቲካ ባሕል ሞግተው መቀየር የጀመሩት ግን በዘማናዊት ኢትዮጲያ ጉልህ ለውጥ የሚባለው ከ*2008 *ዓ.ም ወዲህ የመጣው ነው።*

**መ. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ከ2008 ዓ.ም በኋላ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያቆጠቆጠ የመጣው የፖለቲካ ባሕል ሁለት ውጤቶችን አስከትሏል። አንደኛ ዜጎች በተለይ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚይዙትን ሥፍራና ተሳትፎ በተመለከተ

ያላቸው ዕውቀት፤ ስሜትና አስተያየት በመሰረቱ በመቀየር ላይ ነው። ሁለተኛ ቀደም ሲል በልሂቃን ሰሪ ፈጣሪነት በየአካባቢው ተፈጥረው የነበሩ ተጻራሪ የፖለቲካ ንዑስ ባሕሎች ዛሬም የሃገሪቱ ተግዳሮት ናቸው (*Lovise, 2006)*።

ከላይ እንደተጠቀሰው በቀድሞ ዓመታት በአብዛኛው በክልል ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥነው የፖለቲካ ባህል አሁን በሀገራዊ ጉዳይ ይበልጥ የመሳተፍ አዝማሚያ በዕውቀትም፤ በስሜትም በአመለካከትም ሰፊ ሕዝባዊ መሰረት አግኝቷል። እናም አዲስ የፖለቲካ ባሕል በማቆጥቆጥ ላይ ይገኛል። ቀደም ሲል ለምሳሌ ስለ ኢህአዴግ የኃይል አሰላለፍና አሰራር እንዲሁም ስለፌደራሊዝም የመንግሥት ቅርጽ የዳር ተመልካች የነበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች አሁን ስለነዚህ ጉዳዮች ያላቸው ዕውቀት፤ ስሜትና ድምዳሜ በአስደናቂ ሁኔታ በመቀየር ላይ ነው። የሀገራዊ ውሳኔዎችን ምንነትና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ ያለው የሚሊዮን ዜጎች እና የተገለሉ ክልሎች ፖለቲካዊ ተሳትፎም በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ለዚህ የፖለቲካ ባሕል መለወጥ ምክንያት የመገናኛ ብዙሃን በዘመናዊም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ የታዩት ተሳትፎዎች የዲያስፖራ ሚዲያዎችን ጨምሮ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሁለተኛና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መስፋፋት ያበረከቱት ሚና በቀላሉ አይታይም። የፖለቲካ ባሕሉ እየተቀየረ መምጣቱ ግን ፍጹማዊ መልክ አለው ለማለት አይቻልም። አሁንም ተጻራና ተገዳዳሪ የፖለቲካ ንዑስ ባሕሎች በአንዳንድ ኃይሎች አልጠፉም።

## የኢህአዴግ ልማታዊ መንግሥት እሳቤ

በባለፉት 27 ዓመታት ግን የገበያ ጉድለትን ለመከላከል በሚል ዕሳቤ መንግስት አንድም ከሚገባው በላይ የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴ በሚያቀጭጭ መልኩ ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ሲገባ የነበረ ሁለትም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካለመወጣቱ የተነሳ የመንግስት ጉድለት እንዲከሰት እና በአጠቃላይ ደግሞ የስርዓት ጉድለት በኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ እንዲፈጠር አድርጓል *(Nolawi፣ 2013).* ። ነገር ግን ከፍተኛ የሆነ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ተመዝግቧል።

ኢህአዴግ በተከተለው የፖለቲካ ስርዓት አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ልማታዊ መንግሥት በገበያው የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት የሚፈቅዱ እንደመሆናቸው መጠን በአንጻራዊነት ከካፒታሊዝም በተሻለ አብረው ሊሄዱ የሚችሉ እሳቤዎች ናቸው። ነገር ግን ልማታዊ መንግሥት እሳቤን ተግባራዊ ለማድረግና የሚፈለገውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ መሠረታዊ ባህሪያትን ኢህአዴግ ከተከተለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ተፈጥሯዊ ባህሪን ሟሟላት ይሳነዋል። በዚህም የተነሳ እስካሁን ባለው ትግበራ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማታዊ መንግሥት ግቦችን በተሟላ መንገድ ማሳካት አልተቻለም።

ኢህአዴግ በሕዳር ወር 2003 ዓ.ም *"የተሃድሶ መስመርና የኢትዮጵያ ህዳሴ"* (ገፅ 81-82) በሚለው ጽሑፍ ላይ የሌሎች የልማታዊ መንግሥታት ተሞክሮዎችን በመቀመር ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪያት ጋር በማጣመር የድርጅቱ መመሪያ መሆኑን እና ልማታዊ

ዴሞክራሲ የዘመኑ ብቸኛው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መገለጫ ሆኖ ሊከሰት የሚችልበትም ብቸኛ መንገድ ነው በማለት አስቀምጧል።

> የተሀድሶ እንቅስቃሴያችን የልማታዊ መንግስታት ልምድን በመቀመር እና ይህንኑ ከሀገራችን ሁኔታና ከድርጅታን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪ ጋር በማስተሳሰር ልማታዊ እና ዴሞክራሲያዊ መስመር እንዲቀየስ እና የድርጅቱ ይፋ መስመር እንዲሆን ለማድረግ ተችሏል። እናም የድርጅታችን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር እና ባህሪ ሊቀጥል የሚችልበት ብቸኛው መንገድ የልማታዊ ዴሞክራሲ መንገድ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል። የተለመዱትን የልማታዊ መንግስታት ባህሪያትን ያካተተ እና ከድርጅታችን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሚመነጩ ልዩ ባህሪያትን ያቀፈ ይሄው የልማታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን አብዮታዊ ዴሞክራሲ አሁን ባለንበት የዓለምና የሀገራችን ሁኔታ የተከሰተበት እና ሊከሰት የሚችልበትም ብቸኛ መንገድ ነው ማለት ይቻላል። በሌላ አነጋገር ልማታዊ ዴሞክራሲ የዘመኑ ብቸኛው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በስያሜ ረገድ ከላይ በጠቀስነው ሰነድ አብዮታዊ ዴሞክራሲም፣ ልማታዊ መንግስትም ሆነ የተሃድሶ መስመር እንደ የሁኔታው እየቀያየሩ መጠቀም እንደሚቻል አስቀምጧል።

> አብዮታዊ ዴሞክራሲ የድርጅታን ታሪካዊ አመጣጥና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ስለሚያመላክት ትክክለኛ መጠሪያችን ነው። ልማታዊ ዴሞክራሲ የወቅቱን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይዘት የሚገልፅ እና አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚከሰትበት ና እውን የሚሆንበትን ብቸኛ መልክ ስለሚያሳይም ትክክለኛ መጠሪያችን ነው። የተሃድሶ መስመር የሚለውም አገላለፅም ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር በተሃድሶ እንቅስቃሴያችን የተገኘ መሆኑን ስለሚያመላክት የመስመሩ ትክክለኛ መጠሪያ ነው። ሶስቱም መጠሪያዎች ትክክለኛ እና ተገቢ በመሆናቸው ነው እንደነገሩ ሁኔታ እያቀያየርን የምንጠቀምባቸው።

ኢህአዴግ የልማታዊ ዴሞክራሲን ስሙን ብቻ ጥቅም ላይ ቢያውልም መለያ ባሕሪያቱን ግን በሚገባ አልተጠቀመበትም። ስለሆነም የገበያ ጉድለትን ለመከላከል በሚል መንግሥት አንድም ከሚገባው በላይ የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴ በሚያቀጭጭ መልኩ ለከት የሌለው ጣልቃ ገብነት፤ ሁለትም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ ካለመወጣት የተነሳ የመንግሥት ሀብት ያላግባብ እንዲመዘበር እንዲሁም ሁለንተናዊ የሥርዓት ጉድለት በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ላይ አስከትሏል።

በአጠቃላይ ሲቃኝ ልማታዊ መንግሥት (Developmental State) እንደ ርዕዮተ-ዓለም ከመውሰድ ይልቅ እንደ አንድ መንግሥት ሥርዓት አማራጭ የሚወሰድ ነው። የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብና አተገባበር ሁለት ደረጃዎች ይኖሩታል። ከመነሻው ልማታዊ መንግሥታት ከዴሞክራሲ ጋር ብዙ ትውውቅ አልነበራቸውም። በብዙ ሀገሮች

ከዴሞክራሲያዊ መርሆች ጋር ተራርቀው ነገር ግን ልማትን ማፋጠን ላይ በማተኮር ብቻ ወደ እንቅስቃሴ ለመግባት ይሞክራሉ። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ተግባራዊ እየሆነ ያለው የልማታዊ መንግሥት አማራጭ በአብዛኛዎቹ አገሮች የዴሞክራሲ መርሆዎችንም ተግባራዊ ለማድረግ እብዛም ጥረት ሲያደረጉ አልታዩም። በገበያ የሚመራ የኢኮኖሚ ሥርዓትንም የመገንባት አቅጣጫ ተከትሏል። ስለሆነም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደነ ቻይና ያሉ የልማታዊ መንግሥት አማራጭ የሚከተሉ ሀገራት ወደ ሊበራሊዝም ማዕቀፍ ደረጃ ግስጋሴ ላይ ይገኛሉ። በገበያ የሚመራ የኢኮኖሚ ሥርዓት እንጂ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን የተቀበሉ ናቸው ለማለት ያስቸግራል።

## አብዮታዊ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ

ከደርግ መንግሥት ቀጥሎ በኢትዮጵያ በሥራ ላይ የዋለው የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለሦስት አሥርት ዓመታት ተግባራዊ ሆኗል። የፖለቲካ ኘሮግራም በብዙዎች ዘንድ ግራ መጋባትን የፈጠረና ግልፀኝነት የጎደለው ነበር። ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዓላማ ምንነት በተተነተነ መንገድ ራሱን ችሎ ጽሑፍ የተዘጋጀው በ2009 ዓ.ም ለኢህአዴግ አመራር አካላት ግንዛቤ ለመፍጠር በሚል በተሰጠው ሥልጠና ላይ በቀረበው ሰነድ ነበር። በሰነዱም ላይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንነትን እንደሚከተለከው አቅርቦታል።

> አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከቅድመ-ካፒታሊዝም የአመራረት ሂደት በተለይም ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም መሸጋገር ባለባቸው ሕብረተሰቦች አደናቃፊ ኃይሎችን ለማስወገድና የዴሞክራሲና የእድገት ኃይሎችን ለሥልጣን ለማብቃት የሚያስችለው ዴሞክራሲያዊ አብዮት የሚመራበት ንድፈ-ሀሳብ ነው።

በዚሁ ጽሑፍ ላይ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ቋሚ ርዕዮተ-ዓለም ወይም መስመር ሳይሆን ወደ ቀጣይ ሥርዓት አሸጋጋሪ መሆኑን ለማስረዳት "አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድን ተጨባጭ የለውጥ ምዕራፍ ለይቶ ለመምራት የተዘጋጀ የትግል መመሪያ ነው። በአጭሩ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለአንድ መድረክ ብቻ የሚያገለግል ነገር ግን በዘመኑ መተኪያ የሌለው የለውጥ ፕሮግራም ነው።" በሚል ተተርጉሞ እናገኘዋለን።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሳቤ ጥርት ያላለና ፈጠርነው በሚሉት አካላት ዘንድም ግልፀኝነት የሚጎለው ሥርዓት እንደሆነ ማሳያ ከሆኑት አንዱ ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመምጣቱ በፊት ይከተለው የነበረው ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ(ማ.ሌ.ሊ.ት) የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ግብ ከሌኒን እና ከማኦ ፍልስፍና ጋር የሚመሳሰልና የሶሻሊስት ሥርዓትን ለመገንባት ያነገበ መሆኑን ይገልጻል። ሆኖም በታሪክ አጋጣሚ ኢህአዴግ ሥልጣን በያዘበት ግንቦት 1983 ዓ.ም ወዲህ ዓለምን በምዕራብ እና በምስራቅ የርዕዮተ-ዓለም ጎራ ለሁለት ከፍሎ ሲካሄድ የነበረው የቀዝቃዛው ጦርነት በአሜሪካ መራሹ የምዕራቡ ጎራ የበላይነት የተጠናቀቀበት ሲሆን የሶሻሊዝም እሳቤ በሊብራሊዝም(በካፒታሊዝም) አስተሳሰብ የተረታበት ወቅት ነው። በመሆኑም የወቅቱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ለውጥ አድርጌያለሁ

ቢልም ለውጡ በሊብራሊዝም ፖለቲካ ግብ ያደረገና በኢኮኖሚው መስክ ደግሞ የካፒታሊዝም ነጻ ገበያ መርህን ለመገንባት ሙከራ ያረደገበት ነበር ለማለት ይቻላል። በዚህም መሠረት ኢህአዴግ የሶሻሊዝም ስርዓትን ለማስፈን አስቦ ራሱን ከካፒታሊዝም ካምፕ ያገኘ ፓርቲ ነው።

## በኢትዮጵያ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አተገባባር ሁኔታ

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከጅምሩ የወቅቱ ነጻ አውጭ ንቅናቄዎች በጋራ ደርግን ለመጣል ይታገሉ የነበሩ በሂደትም ወደ ግንባርነት የተለወጡ ድርጅቶች ሲመሩበት የነበረ አስተሳሰብ ነው። እነዚህ ድርጅቶች ኢህአዴግን ከፈጠሩ በኋላም የትጥቅ ትግሉ ሲጠናቀቅ በኢትዮጵያ የሶሻሊዝም ሥርዓት ግንባታን ለማሳካት መሟላት የሚገባው ተጨባጭ ሁኔታ የተሟላ ስላልነበር የነባራዊ ሁኔታ ቅድመ ጥናት መሟላት ላይ ክፍተት የነበረበት ነው። ወደ ሶሻሊዝም ሥርዓት ግንባታ የሚደረገውን ሽግግር ለመምራት የሚያስችል ፕሮግራም ሆኖ የተቀረጸ መሆኑን ሰነዶች ይተቁማሉ።

ይሁን እንጂ የትጥቅ ትግሉ እየተገባደደ በመጣበት ወቅት የዓለም ጂኦ-ፖለቲካ ኃይል አሰላለፉ በመሰረታዊነት ተቀየረ። የሶሻሊዝም ጎራ በመፈራረሱ ምክንያት የካፒታሊስት ጎራ ከሞላ ጎደል ጎልቶ ሊወጣ ችሏል። ይህንኑ ተከትሎ ሶሻሊዝምን በሂደት ለመገንባት መስዋዕትነት የመክፈል ቁርጠኝነት የነበረውና የማርክሲስት ሌኒኒስት ፓርቲ ለመመስረት በግንባር ውስጥ መጠንሰስ ጀምሮ የነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይል እንቅፋት ስላጋጠመው አማራጭ መንገድ ፍለጋውን ተያዘው። ይህንኑ በንድፈ-ሀሳብ ማስደገፍ ስለነበረበት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ወደመንታ መንገድ የሚወስድ ነው የሚል አካሄድ መከተል ተጀመረ።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወደ ሶሻሊዝም ብሎም ወደ ካፒታሊዝም ሊወስድ የሚችል የሽግግር መስመር ነው የሚል የመውጫ ስልት አስቀመጠ። በዚህም በመንታ መንገድ በሚመሰል የሶሻሊዝም መንገድ ሲዘጋ ክፍት ወደ ሆነው የካፒታሊዝም መንገድ በማዞር፣ ሶሻሊዝምን በመተው በነጭ ካፒታሊዝም ማዕቀፍ ጉዞ የሚታይ ከቅድመ-ካፒታሊስት ወደ ዳበረ ካፒታሊስት በሚያደርስ የሽግግር ፕሮግራም በመቀጥል ስሌት ራሱን ከሁኔታው ጋር ለማጣጣም እየሞከረ የነበረ ድርጅት ነበር።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ችግሩ የአቅጣጫ ለውጥ ማድረጉ ሳይሆን ኢህአዴግ ከነጉድለቱም ቢሆን ከወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ራሱን አስማምቶ ለመሄድ የመቻሉ ጉዳይ ነው። ከዓለማዊ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ሁኔታ ራስን ማየት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፕሮግራም መቀየርና የአቅጣጫ ለውጥ ማድረግም ተገቢ ነበር። ሆኖም ጭንብል ማውለቁ ብቻ ሳይሆን ሙሉ ሀቀኛ ማንነቱን ለመረጠው አዲስ አካሄድ ራሱን ሊቀይር አልቻለም። ሶሻሊዝምን ለመገንባት አስቦ ራሱን በካፒታሊስት ሥርዓት ማዕቀፍ የሽግግር ፕሮግራም ሆኖ ያገኘው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ካነገበው ዓላማ በተለየ ሌላ ፍላጎት እንዲያሳካ ተግባራዊ መደረጉ ሀገሪቷን ለበርካታ ውስብስብ ችግሮች ዳርጓታል። ለዚህም

ነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሶሻሊዝም ላይ ለመድረስ አልሞ ነገር ግን በተግባር ራሱን ካፒታሊዝም ሠፈር ውስጥ ያገኘ ባይተዋር አስተሳሰብ ነው ሊባል የቻለው።

### አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ባሕርይው

በኢትዮጵያ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት የተተገበረው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ውጫዊ(explicit) ባሕሪውን፣ ፖሊሲዎቹንና ፕሮግራሞቹን ስንመለከት ኢህአዴግ በመተዳደሪያ ደንቡ የመግቢያ አንቀጽ ላይ ያስቀመጠው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዓላማዎች ዴሞክራሲያዊ ናቸው ይላል። ይሁን እንጂ ውስጣዊ(Implicit) ባሕሪው ግን ከዲሞክራሲያዊ ባሕል ተሞክሮ ያፈነገጠና ኢ-ዴሞክራሲያዊነትን የተላበሰ ነው።

ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለምን በመከተል የሕግ የበላይነትን አስጠብቃለሁ ስለሆነም ሁሉም ነገር ከሕግ በታች መሆን አለበት ይላል። ነገር ግን በወረቀት ላይ ጥሩ የሚመስሉ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቢያወጣም በውስጣዊ ባሕሪው ደግሞ ሕጎችን ያላግባብ መጠምዘዝን ተክኖበታል። በምሳሌ ለማረጋገጥ እንደ የፀረ-ሽብር፣ የፕሬስ እና የሲቪክ ማሕበራትን በተለመለከተ ያወጣቸው አፋኝ ሕጎች ሕገ መንግሥታዊና ሰብዓዊ መብቶችን በተደራጀ ተቋማዊ መንገድ የጣሰበት ነው።

ነፃ እና ገለልተኛ የሆኑ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ የሲቪክ ማሕበራት እንዲኖሩ ያሉትም እንዲጠናከሩ ስለማይፈልግ የውክልና ዴሞክራሲ የማዕዘን ድንጋይ የሆኑት የሥልጣን ክፍፍል *(Division of power)* እና የሥልጣን ቁጥጥር *(Check and balance)* ተግባራዊ እንዳይሆኑ አድርጓል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሕገ መንግሥቱ ላይ እንደተቀመጠው የግልና የቡድን መብት አስጠብቃለው ቢልም በቡድን መብት ስም መማልና መገዘት በተግባር ቡድኖችን በዘውግ ተኮር ልዩነትና አድልኦ ያስተናግዳል። የግል መብቶችን አስከብራለሁ ይላል በተግባር ግን የአፈና ሥርዓት ሲዘረጋ የኖረ ርዕዮተ-ዓለም ይከተላል። በተጨማሪም በሕገ መንግሥት የተቀመጠውን የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በሚቃረን ሁኔታ አንድ አውራ ፓርቲ የበላይነት የሰፈነበትና ጠንካራ ማዕከላዊ ዴሞክራሲያዊነት ሲገነባ ኖሯል።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሌላው ኢ-ዲሞክራሲያዊ ባሕሪ ሚዲያውን ተቆጣጥሮ ለአንድ የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ዕድገት እንደሚሰራና የወታደራዊው ደርግ አገዛዝን በትጥቅ ትግል መጣሉን በነጋ ጠባ ሕዝቡን በማደንዘዝ ቅቡልነትን *(Legitimacy)* ለማግኘት ሲታትር መቆየቱ ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት በማምጣት ቅቡልነትን ማግኘት በራሱ ስህተት ባይሆንም በተቃራኒው የዜጎችን ቁሳዊ ፍላጎት ብቻ ማሟላት በቂ ነው ብሎ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን መጣሱ ትልቁ ስህተት ተደርጎ ይወሰዳል። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አሰላለፍ እነዚህን የሰው ልጅ ፍላጎቶች ችላ በማለት የሁሉም ነገር ትኩረት ድህነት ላይ ብቻ እንዲያጠነጥን ማድረጉ መጠነኛ ለውጥ ቢያስገኝለትም አስተሳሰቡን ሙሉ ለሙሉ ከውደቀት አልታደገለትም። ከዚህ በላይ ሌሎች የከፉ ችግሮችንና መፍትሄዎችን አስተሳስሮ ማየት ባለመቻሉ በሀገሪቱ ለበርካታ ሰብዓዊና ማሕበራዊ ቀውሶች መፈጠር ምክንያት ሆኗል። አስመዘግቤዋለሁ የተባለው የኢኮኖሚ ዕድገትም ጥራት የጎደለው ሲሆን ሀገሪቷን

ከፍተኛ ዕዳ ውስጥ የከተተ የተዛባ የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመጭው ትውልድ ከባድ ሸክም ያስከተለ ነው፡፡

ሌላው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተፈጥሯዊ ባሕሪ በፓርቲና በመንግሥት መካከል ፍፁማዊ አንድነትን ወይም መደባለቅን የጨመደደ ነው፡፡ ኢህአዴግ የመንግሥት ተቋማትን እና አንዳንድ የሲቪክ ተቋማትን የፓርቲው ጉዳይ ማስፈፀሚያ መሳሪያ አድርጎ መጠቀሙን እንደማሳያ ለመጥቀስ ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ የመንግሥት ሠራተኛውን እንደ ፓርቲ አባልና ደጋፊ በመቁጠር የፓርቲውን ግብና ዓላማ ማስፈጸሚያ ስልት አድርጎ ይጠቀምበት ነበር፡፡ በሌላ በኩል የፓርቲውን ዓላማ የሚቃወም ወይም ጠያቂ የሆነ ሠራተኛ ከመታሰር እስከ ሥራ መባረር ብዙ ፈተናዎችን እንዲቀበል ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የመከላከያና የደህንነት ክፍሉ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠው ገለልተኝት ወደ ጎን በመተው የፓርቲው ዓላማ ማስፈፀሚያ መሳሪያ ሆኖ የሚያለግል መሆኑ ነው፡፡ በ2005 ዓ.ም *"የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ"* በተሰኘው መጽሐፍ ላይ በገጽ 25 እና 26 ከሰፈረው ላይ የሚከተለው ሀሳብ አስረጂ ነው፡፡

> *በእኛ ተጨባጭ ሁኔታ የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓታችንን ደህንነት መከላከል ማለትና የሀገር ደህንነት መከላከያ ማለት በመሰረቱ አንድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ከሌለ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህብራዊ ልማት፣ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ወዘተርፈ አይኖርም፡፡ ይህ ከሌለ ደግሞ ሀገሪቱ መጨረሻ ወደ ሌላው ቀውስና ግጭት ገብታ መበታተን ነው፡፡ ስለሆነም ሀገሪቱ እንደሀገር መቀጠል የምትችለው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ ሀገራችንን መከላከልና አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ስርአትን መከላከል አንድና የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡*

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሁሉም ተቋማት በአስተሳሰብ ቅኝት መመራት አለባቸው ብሎ የሚያምን ና እምነቱንም በተግባር ለመተርጎም መንግሥታዊ መዋቅሩን ጭምር በመሳሪያነት በስፋት ተጠቅሟል፡፡ ከሞላ ጎደል ሁሉም ተቋማት ማለት በሚቻል ደረጃ የመንግሥት ሦስቱ ቅርንጫፎች፣ የሕዝብ አደረጃጀቶች፣ የሲቪክ ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት የመሳሰሉት ለአስተሳሰቡ ልዕልና የሚሰሩ የርተ-ዓለም ማጠንጠኛ ማዕከላት ሆነው እንዲያገለግሉ ያደረገ ሥርዓት ነው፡፡

በሁሉም ተቋማት ጉዳይ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመግባት አሰራራቸውና አመራሩ አስተሳሰቡን እንደቅቡል አሰራር እንዲወስድ ካልሆነ ደግሞ የማይቃረን እንዲሆን ለማድረግ በጥብቅ የሚተጋ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ጊዜያዊ ውጤቶችና ጥቅሞችን ቢያገኝም በተቃራኒው ደግሞ ቋሚና ዘላቂ ፍላጎቱ ላይ የተኣማኒነት ጥያቄዎች እንዲነሳበትና እንዳይሳካ አድርጎበታል፡፡ በሁሉንም የመቆጣጠር አባዜ ምክንያት ለመንግሥታዊ ጥንካሬ ገለልተኛ መሆን በሚገባቸው ተቋማት ላይም እጁን ስለሚያስገባ በሕዝብ ዘንድ የተቋማቱ ተኣማኒነትና ተቀባይነታቸው ጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ፣ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ እምነት

እንዳያሳድር፣ በኢትዮጵያ ጠንካራና ገለልተኛ ተቋማት እንዳይገነቡ ብሎም ፖለቲካዊ ችግር በተከሰተ ቁጥር ሀገረ መንግሥቱን የሚያናጋ ሆኗል።

## አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የብሄር ፌደራሊዝም

በተማሪዎች ንቅናቄ ከተነሱት ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች መካከል የብሄር ማንነት ጥያቄ አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያ "የብሄረሰቦች እስር ቤት ናት" ትንተና እንደ መፍትሄ ራስን በራስ የማስተዳደር እስከ መገንጠል የሚል ትርክትን ያዘለ ነው። ይህ ጥያቄ ከሞላ ጎደል ከ1983 ዓ.ም የሥርዓት ለውጥ ጋር ተያይዞ በሕገ መንግሥቱ የፌደራል አወቃቀር ተመልሷል ተብሎ ይነገራል። ይህ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተው ዘውግ ተኮር ፌደራሊዝም የሶሻሊስት መሰረታዊ መርሆን በሌኒን የብሄሮች ራስን በራስ የማስተዳደር እስከ መገንጠል መብት *"The Right of Nation, Nationalities Self-Determination up to Secession"* በሚተነትነበት መጽሐፍ መነሻ በማድረግ ነው። የፌደራሉ ሕገ መንግሥት በደነገጋቸው እንደ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍትሃዊ የሥልጣን ክፍፍል፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ፣ ዴሞክራሲ ተቋማትን መገንባት የሚባሉትን መርሆችን የሚጣረስ የዜጎችን ተሳትፎ የሚገድብ፣ የመድብለ ፓርቲ ፖለቲካን የማያበረታታ፣ ፍትሃዊ የሥልጣን ክፍፍል ለክልሎች ያለመስጠት እንዲሁም እውነተኛ ሳይሆን የይስሙላ *"የምግዚት"* ወይም *"እኔ አውቅልሀለው"* አሰራር ተግባራዊ አድርጓል።

## የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጥንካሬና ድክመቶች

አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደፕሮግራም በኢትዮጵያ ተግባራዊ በሆነባቸው ሰላሳ ዓመታት የተለያዩ ትችቶች ይቀርቡበታል። አንዳንዶች ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲያዊና ለሀገር ያልጠቀመ ብለው የሚከራከሩ ሲሆን ደጋፊዎች ደግሞ መተኪያ የሌለው ፕሮግራም እንደሆነ ሲያነሱ ቆይቷል። ሁለቱንም ጫፎች በመተው ትክክለኛውን ግምገማ ማስቀመጥ ለቀጣይ ጉዟችን ያግዛል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ስንመለከት የተገበርንበትን መንገድ እንደማንኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብ የራሱ ጥንካሬዎችና ህጸጾች ይስተዋሉበታል።

በኢትዮጵያ ከ85 በመቶ በላይ ሕዝብ በግብርና ለሚተዳደር ሲሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይህንን የፖለቲካ መስመር እከተላለሁ ማለቱ በጥንካሬ ሊታይ ይችላል። የአርሶ አደሩን ህይወት ለማሻሻል የተደረጉ በርካታ ጥረቶች በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

በግብርናው ልማት ዘርፍ የተመዘገቡ ተከታታይ ዕድገትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች በስኬት ደረጃ ውጤቶች ቢባሉም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ንድፈ ሃሳብም ሆነ ትግበራ በርካታ ህጸጾችም አሉት። ውስጣዊ ተቃርኖዎችና በአተገባበር ደረጃ የተሰሩ ስህተቶች በጅማሬው የነበረው የንድፈ ሃሳብ ተቀባይነት በሂደት ጥያቄ እየተነሳበት ቀጥሏል። ከተስተዋሉ ዋና ዋና ህጸጾች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው።

- ***ስለ ልሂቃን ያለው ዕይታ መጣረስ***፡- ውስጣዊ ተቃርኖ በፓርቲው ወይም በመንግሥት ውስጥ ያሉ "ተራማጅ" የፖለቲካ ልሂቃንንና በግሉ ዘርፍ ያሉ የኢኮኖሚ ተዋናዮች አተያይ የተዛነፈ ነው። በሀገሪቱ የገበያ ጉድለት መኖሩን በመገንዘብ ስግብግብ ራስ ወዳድነትና ግለሰባዊ የሀብት ጥም ፍትሃዊ የሀብት ድልድልን እንደማይፈጥር በመገንዘብ መንግሥት በገበያ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ሲያስገድድ በተቃራኒው ደግሞ የፖለቲካ ልሂቃኑ ለራሳቸውን ሰፊው ለአርሶ አደር የሚያስቡ፣ ከራስ ወዳድነት የራቁ እና "የበራላቸው" አድርገው መቁጠራቸው የሚቃረን ነው። በሂደት እንደተስተዋለውም በመንግሥት ጉድለት ምክንያት የተፈጠረው ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት የሕዝብን ጥቅም በግል ጥቅመኞችና በመንግሥት ብልሹ አሰራር ምክንያት ሊነጠቅ እንደሚችል መስተዋሉ ነው። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ የቡድን መብት ይጋፋሉ ያላቸውን ልሂቃን በጥብቅ ቁጥጥር ተጠያቂ ለማድረግ ጫና ቢፍጠር የሚፈልገውን ማሳካት አልቻለም።
- ***ኢኮኖሚያዊ አላካኪነት የተጫነው መሆኑ***፡- አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሶሻሊዝም ውሉድ ስለሆነ መሠረታዊ እሳቤው ኢኮኖሚያዊ አላካኪነት የተጫነው ነው። ይህ ሲባል ችግሮችን ሁሉ ከኢኮኖሚ ጋር የማገናኘት ወይም የማላከክ ዝንባሌ ነው። ሶሻሊዝም የሕብረተሰቡ ላዕላይ መዋቅር ማለትም የፖለቲካ፣ የሕግ፣ የባሕል፣ የምርት ግንኙነት እንዲሁም በአጠቃላይ የኢኮኖሚው መዋቅር ውጤት ነው ብሎ ያምናል። ስለሆነም የፖለቲካም ሆነ ሌላ ችግር ምጣኔ ሀብታዊ ውጤት ናቸው ብሎ ያስባል። ነገር ግን የሰው ልጅ ህይወት በምርት ግንኙነት ብቻ የታጠረ አይደለም። ሠራተኛው ወደ ኢንዱስትሪ ወይም ሌላ የሥራ ቦታ ሲሄድ በሠራተኛነቱ የሚኖረው ማሕበራዊ ሥፍራ እንዳለ ሥራ ቦታ ይወስደዋል። ከምርት ግንኙነት ባሻገር ቤተሰባዊ ግንኙነትና ሌሎችም ግንኙነቶች የሰዎችን ውሎ በመወሰን ልዩ ልዩ ማሕበራዊ ሥሪቶች እንዲኖሩ ያደርጋሉ።

ከዚህ ኢኮኖሚያዊ አላካኪነት ልማድ የመጣው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ልማት ላይ ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ ሀገሪቱ ተከታታይ ነውጥ የምታስተናግደው በድህነት ብሶት ምክንያት ነው ይላል። ሆኖም ይህ የጉዳዩን አንድ ገጽታ ብቻ የሚያሳይ ምልከታ ነው። ዜጎች በድህነት ምክንያት ተማረው ለግጭትና ነውጥ የሚነሳሱ ቢሆንም በአንጻሩ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የተደረገው ጥረት ግጭትን ቀንሶ ዘላቂ ሰላም ሊያመጣ አልቻለም። ይህም ዜጎች ማሕበራዊ አገልግሎቶች ስላገኙ ብቻ ሰላም ይሰፍናል የሚለው አስተሳሰብ የተሳሳተ መሆኑን በተግባር ለማየት ተችሏል።

የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሳት የሚለየው ነገር ከቁሳዊ ፍላጎቶች የዘለሉ ፍላጎቶቹ ናቸው። እነዚህም ነጻነት፣ ሰብዓዊ መብት፣ ፍትሕ፣ እኩልነት፣ ሃሳብን በነጻነት የማራመድ መብት፣ የመሳሰሉት ናቸው። አንድ ሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች(ምግብ፣ ቤት፣ ልብስ፣ ትራንስፖርትና መዝናኛ) ስለተሟላለት ከለውጥና ከነውጥ ነጻ ሊሆን አይሆንም። ከእንስሳዊ ፍላጎቶቹ መሟላት አስቀድሞ ሰብዓዊ ጉዳዮች ችላ የማይባሉ ናቸው። የዜጎቻቸውን ቁሳዊ ፍላጎት በምጣኔ ሀብታቸው ብዛት ለማሟላት የጣሩ አምባገነን መንግሥታት ሕዝባዊ ተቃውሞ በየጊዜው አጋጥሟቸዋል። በተለይም ድህነትን ከማሸነፍ ባሻገር የነጻነትና ፍትሕ ጥቄዎች ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

- ***አሸጋጋሪ መስመርነቱን ትቶ ቋሚ መሆኑ፡-*** *አብዮታዊ ዴሞክራሲ አሸጋጋሪ ፕሮግራም ሆኖ ሳለ እንደ ቋሚና ዘላቂ ርዕዮተ-ዓለም ኢህአዴግ መቀበሉ ዋነኛ ችግር ነው። በኢህአዴግ ሰነዶችም ጭምር እንደተቀመጠው አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ኮሙኒዝምና የከበርቴ ሥርዓት ራሱን በቋሚነት ለመትከል የሚሠራ ርዕዮተ ዓለማዊ የመንግሥት ሥርዓት አይደለም። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ግብ በቅድመ-ካፒታሊስታዊ ደረጃ ያለ ሀገር ወደ ካፒታሊስታዊ ሥርዓት እንዲሸጋገር በማድረግ የተሟላ ዴሞክራሲና ፍትሃዊ ኢኮኖሚ የነገሠበት ማሕበረሰብ መገንባት ነው። በዚህም ሁኔታ ርዕዮቱ በአጭር ጊዜ ከስሞ በሶሻል ዴሞክራሲ እንደሚተካ አስቀምጧል።*

*በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ካፒታሊስታዊ ሽግግርን የማዋለድ ተልዕኮ ለሽግግሩ የሚያስፈልጉ ቀዳሚ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ዕድገቶችን በሚገባው ልክ ማምጣት አልቻለም። የሀገራችን ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የተሰሩ ሥራዎች ካፒታሊዝምን ከመገንባት አንጻር ምን ያህል ውጤታማ ነበሩ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ይህንን በተሻለ መልኩ ለማየት በተደራቢነት ተግባር ላይ የዋለውን ልማታዊ መንግሥት ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ምንነት በቅድሚያ ማየት ይገባል።*

*ልማታዊ መንግሥት የሩቅ ምሥራቅ እስያ ሀገራት ተኣምራዊ የሚባል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲያስመዘግቡ ያስቻለ አማራጭ ነው። ልማታዊ መንግሥት ልክ እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የመሸጋጋሪያ አስተሳሰብ ሲሆን በዋነኝነት መንግሥት ኢኮኖሚውን በማነቃቃት ለግል ባለ ሀብቶች ምቹ ምህዳር ለመፍጠር የሚያስችል ነው። በሌላ በኩል በተመረጡና የግሉ ባለሀብት ሊገባባቸው በማይችል በአጭር ጊዜ ብዙ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ እንዲሁም በቀጣይ ለግሉ ዘርፍ ዕድገት መደላድል በሚፈጥሩ መስኮች ላይ መንግሥት በንቃት እንዲሳተፍ በማድረግ ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት ያለመ ነው። ሆኖም በዚህ ርዕዮተ-ዓለም ትግበራ የተመዘገበው ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በመልካም ጎኑ የሚነሳ ቢሆንም በሚፈለገው ደረጃ ነጻ ገበያ መመሥረትና ጥገኛ ያልሆነ የግል ዘርፍ መገንባት አልተቻለም። ለዚህም ምክንያቱ የመንግሥት ጉድለት መንሰራፋትን ተከትሎ ኢኮኖሚ በጥቂት ኃይሎች ቁጥጥር ሥር መውደቁና የመንግሥትን ሀብት የሚቀራመት በመረብ የተሳሰረ ባለሀብት መፈልፈሉ ነው። በራስ ጥሮ ግሮ ሀብት ለማፍራት ለሚተጋው ባለሀብት ግን በሩ ዝግ ሆነበት። መንግሥት ቀስ በቀስ ከገበያው እየወጣ ይሄዳል የሚለው መርህ ተዘንግቶ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በፕራይቬታይዜሽን ወደ ግል ከዞሩት ተቋማት የሚበልጡ ተቋማት እንደገና ተቋቋሙ። በብረታ ብረትና በመሰል ግዙፍ ዘርፎች እንዲሠማሩ የተቋቋሙት ተቋማት ቴሌቭዥን መገጣጠም ጀመሩ ተብሎ የመፈንደቅ ፕሮፖጋንዳ ተጠናወታቸው።*

*መንግሥት በልማት በኩል በሚያደርገው ጥረት ውስጥ የመንግስት ሚና በግሉ ባለሀብት እየተተካ የሚመጣበትንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑ ጠንካራ ባለሀብቶችን ለማፍራት ያስቀመጥነው ትልም ተጨናግፎ በሂደቱ የግሉ ባለሀብት በመንግሥት እየተገፋ እንዲቀጭጭ ሆኗል። ይህ የሚያደርገውን የገበያ ጣልቃ ገብነት*

እንደምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ዘርፋቸውን የሚያጧጡፉ የመንግሥት ጥገኛ ልሂቃን ጥቅማቸው እንዳይቀርባቸው በሚያደርጉት ጫና ነው።

መንግሥት ሚናውን ለግል ባለሀብቱ እየለቀቀ ከመጣ እነዚህ በመንግሥት ስም የሚዘርፉ ጥገኛ ግለሰቦች ጥቅማቸው ስለሚነካ በቻሉት አቅም የግል ባለሀብቱ እየቀጨጨ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት እንዲጨምር ፍላጎት አላቸው። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይህን ዝርፊያ ለመቆጣጠር የሚያስችል ነጻ የሕግ ሥርዓት ስላልዘረጋ የሕግ የበላይነትን ማስፈንና ዘራፊዎቹ ሕጉን እንደ መሣሪያ በመጠቀም የዝርፊያ መረባቸውን ሊያጠናክሩበት ችለዋል።

በአብዮታዊ ዴሞክራሲም ሆነ በልማታዊ መንግሥት እሳቤ ወቅት የተዘነጋው ጉዳይ መሸጋገሪያ ድልድይ መሆኑን መዘንጋቱና ሽግግር ሳይካሄድ ባለበት እንዲቆም መፈለጉ ነው። መሸጋገሪያ የተባለው ራሱ መዳረሻ ሆኖ ቀረ። ሽግግሩን በቶሎ አጠናቆ ወደ ቀጣዩ ማህበረሰባዊ ደረጃ ያለመሸጋገር በፖለቲካው መስክ ለአርሶ አደሩ የሞግዚትነት ካባ እንዲሁም በኢኮኖሚው ደግሞ ዋና ዋና ዘርፎችን የመቆጣጠር ዕድል ለኢህአዴግ ሰጠው።

ይህንን እንደመልካም አጋጣሚ የሚጠቀሙ ባለሥልጣናትና ባለሀብቶች በቻሉት መጠን ድልድዩ ላይ ቆመው ለእነርሱ ብቻ የሚበጀውን ጥቅም እንዲያሳድዱ አመቻችቶላቸዋል። መሸጋገሪያይናል የተባለው የርዕዮተ-ዓለም ድልድይ ከተፈቀደለት ክብደትና ጊዜ በላይ ለመሸከም በመገደዱ መነቃነቅና መሰነጣጠቅ ጀመረ። በመጨረሻም ፖለቲካዊና ሀገራዊ ህልውናችንን የሚፈትን አዘቅት ውስጥ ተዘፍቀን።

ግብርናችን በፍጥነት ሽግግር እንዳያደርግ የተማረው የገበሬ ልጅ በፍጥነት ወደ ጎጆ ኢንዱስትሪና ቀጥሎም ወደ መካከለኛ ደረጃ አምራችነት እንዳያድግ በመንግሥት ከታቀዱ ዘርፎች ውጭ ባሉ ፈጣን ዕድገት ሊያስመዘግቡ በሚችሉ ዘርፎች መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች የብድርና ድጋፍ አቅርቦቶችን እንዳያገኙ ይከለክላል። በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ከመንግሥት ኢንቨስትመንት ባሻገር በሰፊ መሠረት ላይ እንዳይቆም አድርጎታል ለማለት ያስደፍራል።

- ***ሕገ መንግሥታዊ መድብለ ፓርቲ ሥርዓትን በአውራ ፓርቲ የተካ መሆኑ፡-*** *ኢህአዴግ ያፀደቀው ዘር ተኮር ሕገ መንግሥት የመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የመገንባት ዓላማ ነበረው ቢባልም በአንጻሩ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኘሮግራም የአርሶ አደሩን ጥቅምና ፍላጎት ላይ የተመረኮዘ አውራ ፓርቲ የማጽናት ነባራዊና ኅሊናዊ ሁኔታ ፈጥሯል። በመሆኑም በተወሰነ በሕዝባዊ ተቀባይነት ምክንያት የፖለቲካ ምሕዳሩ እንዲጠብና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንዲቀጭጭ ሊያደርግ ችሏል። በመሆኑም በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ችግር የሆነው አውራ ፓርቲ የተፈጠረው ቢሮክራሲውን በመቆጣጠርና በረቀቀ መንገድ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በመደፍጠጥ በተጽዕኖ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ከሕገ መንግሥቱ ጋር በእጅጉ የሚቃረን መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።*

በ1980ዎቹ የነበረው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባት ጅምር ሂደት ከነበረበት አካታች ሁኔታ ቀስ በቀስ የፖለቲካ ምሕዳሩን ወደሚያጠብ ሁኔታ እየተንሸራተተ ሄደ። ብዝሃነት

መሠረታዊ እውነታ በሆነበት ሀገር በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡ መሠረታዊ መርሆችና ሙብቶች ኮስሰው የማይከበሩና የሚደፈጠጡ መምጣታቸው የአውራ ፓርቲ መደላድልን በመገንባት ማንኛውንም መንግሥታዊ ተቋም የአውራ ፓርቲ አጀንዳን ብቻ የሚያስተጋባ ተደርጓል።

- **በቅድመ-ካፒታሊስት ስልተ-ምርት ላይ ያተኮረና ለሌሎች ስልት-ምርቶች ትኩረት ያልሰጠ መሆኑ**፡- በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያዩ ስልተ-ምርቶች እንደመኖራቸው መጠን ከኢኮኖሚያዊ ገጹ ጋር የተያያዘው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ህጸጽ በቅድመ-ካፒታሊስት ስልተ-ምርት ላይ ያተኮረና ለሌሎቹ ስልተ-ምርቶች ትኩረት ያልሰጠ መሆኑ ነው። ካለፈው ሥርዓት ተሸጋግረው የመጡ ወይም ገና እየተፈጠሩ ያሉ ስልተ-ምርቶች ከዋናው ስልተ-ምርት ጋር ተሰናስለው ካልታዩ የሀገሪቱን ማሕበራዊ ሥሪት በአንድ አቅጣጫ ብቻ መቃኘት የተሟላ ሀገራዊ ስትራቴጂ ለመንደፍ ይሳናቸዋል።

  በሀገራችን ከዓለም አቀፍ የገበያ መር ኢኮኖሚና ከቴክኖሎጂ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የካፒታሊስት ስልተ-ምርት እየጎለበተና የሀገራችንንም ማሕበራዊ ሥሪት ሲወስን ቆይቷል። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና በዋናነት በሰፊው አርሶ አደር ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ መፍጠር ላይ ያለውን የካፒታሊስት ስልተ-ምርት በሚገባ ተንትኖ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ አልሆነም።
- **ከጠንካራ የመንግሥት ቢሮክራሲ ይልቅ ጠንካራ ፓርቲ ለመፍጠር መሞከሩ፡-** የልማታዊ መንግሥት ግብ የተቀመጠው ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ልማት ለማስመዝገብ ነፃ፣ ተወዳዳሪና ገለልተኛ የሆነ ጠንካራ መንግስታዊ ቢሮክራሲ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ለመገንባት የልማታዊ መንግስትን ተልዕኮ የሚመጥን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ባለቤት የሆኑ ሠራተኞች፣ የሲቪክ ማሕበራት፣ የፍትሕ እና የዴሞክራሲ ተቋማት ወሳኝ ናቸው። ነገር ግን በሀገራችን ለልማታዊ መንግሥት መፈጠር አስፈላጊ የሆኑ መሰል ተቋማት ተፈጥረዋል ለማለት አያስችልም።

ይህ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የልማታዊ መንግሥት ፈለግ ተደርገው ከሚቆጠሩት የደቡብ ምሥራቅ እስያ ልማታዊ መንግሥታት ተሞክሮ በተቃራኒ የቆመ ነው። ለዚህም የልማታዊ መንግሥት ዋነኛ ጥንካሬ ዘላቂና ጠንካራ ተቋማትንና ቢሮክራሲን መፍጠር መቻላቸው ነው። እያደር የበላይነት ይዞ የመጣው *"ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት"* አመለካከት ይቅርና የ *"አምባገነናዊ የልማት መንግሥት"* የበላይነት ይዞ በነበረበት ዘመን እንኳ ትልቁ ግኝት ጠንካራ ተቋማት መገንባትና በተለይም በችሎታና ከፍተኛ ሀገራዊ ስሜት የተገነባ እንዲሁም ከፖለቲካ ወገንተኝነት የተላቀቀ ቢሮክራሲ ለመፍጠር ተሞክሮ ነበር።

የአሠራር ብልሹነትንና ሕገ ወጥነትን በማጋለጥ ኢ-ፍትሃዊ ተግባራትን የሚዋጉ የሲቪክ ተቋማት፣ ጋዜጠኞች፣ የጥበብ ሰዎች በሙሉ መደበኛ ነጻነታቸውን ተነፍገው

"ልማታዊ" የሚል ቅጥያ እንዲኖራቸውና ሥርዓቱን ያላንዳች ቅራኔ እንዲደግፉ ተደረገ። ይህም መንግሥታዊ የተጠያቂነትና ቁጥጥር አሰራር እንዳይኖር በር የከፈተ ነው።

በመሆኑም ባለፈው በመጣንበት መንገድ የታዩ ጅምሮችን ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ መሄድና የተፈጠሩ ስህተቶችን በአግባቡ ማረም ግድ ይላል። ስህተቶችን ማቆነጃጀት ሀገርና ሕዝብን ለከፍተኛ ጉዳት እየዳረጉ ይገኛል።

- **የፓርቲ እና የመንግሥት ሚና መደበላለቅን የሚደግፍ መሆኑ፡-** አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን እንደ መርህ የተቀበለ እና አንድ አውራ ፓርቲን የመፍጠር ዓላማ ያለው እንደመሆኑ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ የፓርቲ እና የመንግሥት ሚና መደበላለቅን የሚደግፍ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ፓርቲው ባለው ከፍተኛ ሥልጣን የተለያዩ መንግሥታዊ እንዲሁም የሲቪክ ተቋማትን በመጠቀም ግቡን ለማስፈፀም እንደ መሳሪያ ይጠቀምባቸዋል።

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርና ኢህአዴግ መራሹ መንግሥትን ነጣጥሎ ለማየት በሚያስቸግር ሁኔታ አንድና ያው ሆነው እንዲተሳሰሩ አድርጓል። በራሳቸው መቆም የሚገባቸው የፖለቲካ ተቋማት ስለተቀላቀሉ መስመሩን የሚቀናቀን ሁሉም ባይባልም አብዛኛው ሀገረ-መንግሥቱንም በተመሳሳይ የሚቀናቀን እንዲሆን አድርጓል። በመስመሩ የሚፈጠር ችግርና ልዩነት ከድርጅቱ አልፎ ተርፎ ሀገርን ሲንጥ ማየት የተለመደ ነው።

ዜጎች መስመሩንና መንግሥትን ለይተው ለማየት በማይችሉበት ደረጃ ሁለቱ ተቋማት በጥብቅ የተያያዙ ስለሆኑ ሀገረ-መንግሥቱንና የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም መስመሩን ደባልቀው የሚያዩበት አስተሳሰብ ፈጥሯል። በመሆኑም መስመሩን ሲቃወሙ ሀገረ-መንግሥቱንም አብረው ለማፍረስ እንዲሰሩ የሚያስገድድ ሁኔታ በመፍጠሩ ምክንያት ህልውናው ከመንግሥታዊነት ጋር በጥብቅ በማቆራኘት የፓርቲውን እድሜ ለማርዘም የኳተነ ነው። በዚህ ምክንያት አስተሳሰቡ ሲታመም ድርጅቱ ብቻ ሳይሆን የሀገረ-መንግሥቱም እጣ ፋንታ በፅኑ እንዲታመም ለማድረግ ተሞክሯል። ይህም ዜጎች ከዛሬ ነገ ሀገር ልትፈርስ ነው በሚል ስጋት ውስጥ እንዲሰጉበተጨባጭም ሊባል ወደሚያስብል ሁኔታ ውስጥ እንዲወድቁ ያደረገ አስተሳሰብ ሆኖ እናገኘዋለን።

ይህ ብቻ አይደለም ከዴሞክራሲ ጋር በቀጥታ የሚያያዝ ቢሆንም እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሁለቱን ተቋማት ቀላቅሎ በተፈጠረለት የመንግሥት ተቋማትና የፓርቲ ውግንና ተጠቅሞ እንዴት ራሱን በሥልጣን ለማቆየት እንዳመቻቸ ነው። የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት መገንባት ዓላማው አድርጎ አስቀምጦ ነገር ግን በዚህ ማዕቀፍ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሥልጣን እየያዘ ሀገር የመምራት ፍላጎት እንዳለው ይገልጻል በተግባር ግን የተፈጸመው ከዚህ በተቃራኒ ነው። መንግሥታዊ ተቋማትን በመጠቀም ተፎካካሪ ሊሆኑ የሚችሉ ኃይሎችን እያዳከመና በምርጫ ሊያሸንፉ የሚችሉበትን ዕድል እያጠበበ ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በስተቀር በሀገራችን እስከአሁን በተካሄዱ ምርጫዎች ብቸኛ አውራ ፓርቲና የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሆኖ የቆየበት ሁኔታ ፈጥሯል።

ይህንንም በዳበረ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲታይ መስመርን ከአውራ ፓርቲ ክስተቶች ጋር አዛማጆ ቅቡልነት እንዲኖረውና ይህንኑ የማስቀጠል ፅኑ ፍላጎት ነበረው። ይህ አስተሳሰብ ለሀገረ-መንግሥቱ መረጋጋትና ዘላቂነት አስፈላጊ ተደርጎ የሚወሰደው ጠንካራ ዴሞክራሲ ሥርዓት እንዳይገነባ እንቅፋት በመሆኑ በሀገሪቱ ከዴሞክራሲ ጥያቄ መመልስ አኳያ የሚነሱ ተቃውሞዎችን አባብሷል። አስተሳሰቡም ያነጣጠረው በሀገረ- መንግስቱን መቆጣጠር ላይ በመሆኑ ሀገራችን ለአደጋ ያጋለጠና ሁሌም የሚታወስበት/legacy/ እንዲሆን አድርጓል።

በተጨማሪም የፓርቲው መዋቅር ከመንግሥት አደረጃጀት ጋር የመቀላቀል ሙከራ በመደረጉ በተጨባጭ ደካማ ለሆነ ሲቪል ሰርቪስ መፈጠር ምክንያት እየሆነ ሊመጣ ሆኗል። የሲቪል ሰርቪስ መዋቅሩ በዕውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ በብቃት መያዝ ያለባቸውን የሥራ መደቦች ሁሉ በሹመት እንዲሞሉ በማድርጉ አስተሳሰቡ የልማታዊ መንግሥት ባህሪ የተላበሰ ሲቪል ሰርቪስ እንዲሆን ለወትሮው በሙያዊ ደረጃና ብቃትን የሚፈልጉ ሥራዎች እንዲዳከሙ የሲቪል ባለሙያው ተነሳሽነት እየቀነሰና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየወረደ ሕዝብ በመንግሥት ላይ ምሬት እንዲያሳድር አድርጎታል። ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ በአጭር ጊዜ በመገንባት ሀገራቸውን ካሸጋገሩ የልማታዊ መንግሥታት በተቃራኒ የእኛው ሀገር አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ደካማ ሲቪል ሰርቪስ ያስመዘገበ ሆኖ ታይቷል።

- **ምልዑ እይታ የጎደለው አጀንዳ አስቀያሽ አስተሳሰብ፡-** አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሁሉም ችግሮች መንስኤ ርዕዮተ-ዓለም መስመሩን የሚቃረን ነገር ብቻ እንደሆነ የሚያስብ ቁንፅል እይታ ያለው መስመር ነው። ይህ አስተሳሰብ በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል። አንደኛው ነገሮችን በምልዑ እይታ ለቃኘት የሚያስችል የምልከታ መነፅር አልባ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሁሉም ነገር ትኩረት ወደ አንድ ነገር ላይ ብቻ እንዲያነጣጥርና በዚያ ዙሪያ እንዲሽከረከር በማድረግ አጀንዳ የማስቀይስ ስልት የሚከተል መሆኑ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው አመራሩ ሁሉም የሀገሪቱ ችግሮች መንስኤ ድህነት ነው ተብሎ እንዲታመን የቅስቀሳ ፕሮፓጋንዳ ርቀቱን ማየት በቂ ነው።

የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲሟሉለት መስራት አጠያያቂ አይደለም። ይህ ሲባል ግን እንዲያው ለሆዱ ብቻ የሚኖር ፍጡር ነው ማለት አይደለም። ከእንስሳት የሚለየው የራሱ ነጻነትና ክብር ተነፍጌያለው ብሎ ሲያምንም መስዋዕትነት እስከመክፈል የሚያደርስ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ያማከለ ክቡር ፍጡር ነው።

ሆኖም አብዮታዊ ዴሞክራሲ እነዚህን የሰው ልጅ ፍላጎቶች ችላ በማለት የሁሉም ነገር ትኩረት ድህነትና የድህነት አጀንዳ ላይ ብቻ እንዲያጠነጥን ማድረጉ መጠነኛ ለውጥ ቢያመጣለትም አስተሳሰቡን ከውድቀት አልታደገውም። ይልቁንም ሌሎች ችግርና መፍግሔ አስተሳስሮ ማየት ባለመቻሉ በስተመጨረሻው ሲያልቅ አያምር ሆኗል።

በመጨረሻም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ለመገንዘብ የሚቻለው በንድፈ ሃሳብ ቁንፅልነት ራሱን እንዴት ጠልፎ እንደጣለ ነው፡፡

ከነጻነትና ክብር ጋር የተያያዙት ሕዝባዊ ፍላጎቶች ትኩረት ያለማግኘታቸው ከመሰረታዊ የአስተሳሰብ ባህሪ የሚመነጭ ሆኖ ከህሊና ተጠያቂነት ይልቅ አጀንዳ ለማስቀየስ ጥቅም ላይ ሲውል ታዝበናል፡፡ ኢህአዴግ እንዳሰበው ሳይሆን ቢቀርም ስለድህነት ብቻ ሁሉም እንዲዘምር በማድረግ ሌሎች አጀንዳዎች እንዲዳፈኑ ሆነ ብሎ አድርጓል፡፡ የድህነት ዘበኛ ትርክት በማምጣት በተለመደው የጸረ-ልማት ማሸማቀቂያ ፍረጃ ይጠቀም ነበር፡፡ በመሆኑም የዜጎች ክብርና ነጻነት ጥያቄዎችን በማዳፈን ሌሎች የትኩረት አጀንዳ ማስቀየሻ ስልቶችን በስፋት ጥቅም ላይ ያውላል፡፡ ለድርጅታዊ አስተሳሰብ ልዕልና የሚተጋ እሳቤን በመከተሉ ሕዝቡ ራሱን ለማስከበር በተካሄደ የውስጥ ትግል ግብዓተ-መሬቱ ወደመቃረብ ሊደርስ የቻለ አስተሳሰብ ነው፡፡

- **ሕብረተሰብን በልዩ ልዩ ጎራ በመከፋፈል ቅራኔን ማባባሱ፡-** አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከማርክሲስት ባህል የወረሰው ቢኖር አስተሳሰቡ የተገነባው የሕዝብን ብህሃነት በጎራ ከፋፍሎ አንዱን በአንዱ ለቅራኔ ማነሳሳት መሆኑ ትችቶች ይቀርብበታል፡፡ በመሆኑም እወክለዋለው ወይም የርዕዮት-ዓለም ማሕራዊ ዋና መሰረቴ ነው ለሚለው ክፍል በየጊዜው ጠላት ይፈልግለታል፡፡ አብዮታዊ የሆኑ ዘውግ ተኮር ፓርቲዎች በባህሪያቸው ለሕብረተሰብ የጥቅም ተቃርኖ*(conflict of interest)* ያለው ጠላት ይፈልጉለታል፡፡ ከሌላው ማሕበረሰብ ጋር ያለውን መልካም እሴቶችና ግንኙነቶች ወደጎን በመተው ተቃርኖውን አጉልቶ ለዚያ ለሚወክሉት ማሕበረሰብ አደገኛ የታሪክ ጠላት አድርገው በማሳየት ሌላ ሊታደግ የሚችል አካል እንደሌለ በመስበክ ሥልጣኑን ለረዥም ጊዜ ማስጠበቅ እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሕብረትን፣ አንድነትንና መተማመንን በሕዝቡ ዘንድ እንዲጠፉ ብሎም የሚደግፉትን "ልማታዊ" የማይደግፉትን ደግሞ "ፀረ-ልማት" ወይም "ኪራይ ሰብሳቢ" በሚል ታርጋ እያሸማቀቀ እድሜውን ለማራዘም የተጠቀመበት መንገድ ነው፡፡

ይህን በማሳያነት ለማረጋገጥ እንዲረዳን ጥቂቶቹን እንጥቀስ፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስለ ሀገሪቱ ምሁራን ያለው የተንሸዋረረ እይታ ውጤት በተቃርኖ የተሞላ ነው፡፡ ከማርክሲስት ሌኒኒስት ንድፈ ሃሳብ በመነሳት ከመደብ ትንታኔ አኳያ ምሁራንን ወላዋይና የንዑስ ከበርቴ መደብ በሚል ይፈርጃል፡፡

በዚህ የተዛባ አመለካከት ምሁራንን በሁለት ጎራ ከፍሎ ከአንደኛው ወገን ጋር ይወዳጃል ከሌላው ጋር ደግሞ ተቃርኖ ውስጥ ይገባል፡፡ በመጀመሪያው ጎራ የሚፈረጁት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አቀንቃኞችና ደጋፊዎች ሲሆኑ ተራማጅ ወይም አብዮታዊ ምሁር ብሎ ይገልፃቸዋል፡፡ በሁለተናው ጎራ የሚፈርጃቸውን ደግሞ ልማታዊ ያልሆኑ ወይም ኪራይ ሰብሳቢ ምሁራን ይላቸዋል፡፡ በሁለቱ መካካል ያለውን ልዩነት ሲያስቀምጥም ተራማጅ ምሁራን ለጭቁኑ ወገን የቆሙና ከራሳቸው ጥቅም አስበልጠው የሕዝብን ጥቅም የሚያስቀድሙ አድርጎ ያያል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ገለልተኛ ምሁራንን ደግሞ

ለግል ጥቅም የሚሯሯጡና የሕዝብን ጥቅም አሳልፈው የሚሰጡ ራስ ወዳድ እያለ በዐይነ ቁራኛ ይመለከታቸዋል።

ይህ የተቃርኖ ፍረጃ በግል ባለሀብቱም በተመሳሳይ መልኩ የሚጠቀምበት ሲሆን ልማታዊ ባለሀብትና ኪራይ ሰብሳቢ ባለሀብት በሚል ይገለጻል። ለሕብረተሰቡ ግልፅ በማይሆን ድርጅታዊ መስፈርት ጥቂቶች የልማታዊነት ካባ ተደርቦላቸው ኢ-ፍትሃዊ ጥቅማ ጥቅም ይመቻችላቸዋል። በየመንግሥት ተቋማቱ ከጡት አባቶቻቸው ጋር ትስስር ራሳቸውን ሲያበለጽጉና ሀገር ሲያራቁቱ ተስተውሏል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከልማታዊ ዴሞክራሲ ጋር ያው አንድ ነኝ ብሎ ሲያበቃ በተግባር የታየው ግን ከላይ እንደተገለጸው ሙስናንና ሌብነትን ያስፋፋ ፍረጃ የወዳቂ አስተሳሰብ ውጤት መሆኑን ነው። በሌላ በኩል ከባለሀብት አኳያ ሊታይ የሚገባው ለሀገር ውስጥ የግል ባለሀብትና ለውጭ ባለሀብት ያለው አመለካከት ቃሉ ከተግባሩ የማይገጥም መሆኑ ነው። ለሀገር ውስጥ ባለሀብት ልዩ ትኩረትና ድጋፍ እንደሚሰጥ ያስቀምጥና በተግባር የውጭ ባለሀብቶች ላይ በኢንቨስትመንት ስም ለዘረፋ እያመቻቸ ሙጭጭ ይላል። ለሀገር ውስጥ የግል ባለሀብቶች በሚገባላቸው ቃል መሰረት ድጋፍ ስለማያገኙ የግል ዘርፉ እንዲቀጭጭ ማድረጉ ይታወቃል።

ባለፉት 27 ዓመታት አህአዴግ የርዕዮተ-ዓለም ማሕበራዊ መሰረቴ ጭቁን አርሶ አደር ነው እያለ በተግባር ግን አስተሳሰቡን በይፋ ሳይቀይር ለነጭ ካፒታሊዝም አመቻችቷል። በተለይም በኢህአዴግ ውስጥ አድራጊ ፈጣሪ የነበረው ሕወሓት/TPLF በትጥቅ ትግል ዘመኑ ታገልኩለት የሚለው መርህ መደባዊ ሳይሆን የብሄር ማንነት ላይ የተመሰረተ የሶሻሊዝም መርህ ነበር። በ1983 ዓ.ም ርዕዮተ ዓለሙን ከሶሻሊዝም ወደ ነጭ ካፒታሊዚም ሲቀይር አካሄዱን ወደ መደባዊ ትግል በመለወጥ ማሕበራዊ መሰረቱ የሀገሪቱ አርሶ አደሮች መሆናቸውን ይገልጻል። አርሶ አደሩን ወደ መካከለኛ ገቢ ለማድረስ ለግብርናና ገጠር ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራም ይደሰኩራል። የግብርና-መር ኢኮኖሚ ለገጠሩ አርሶ አደር የምግብ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን ለኢንዱስትሪው ግብዓት ጥሬ እቃ የሚያቀርብ እንዲሆን በፖሊሲውና ስትራቴጂውም ላይ ዕቅዱን አመላክቶም ነበር። ኢህአዴግ የገጠሩን አርሶ አደር ማሕበራዊ መሰረት እንደማድረጉ መጠን ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለገጠር ልማት ቅድሚያ መስጠቱ ተገቢ ቢሆንም ዕቅዱ በማምረቻ ቴክኖሎጅና ግብዓት ችግር የተነሳ ውጤታማ አልሆነም። በተጨማሪም የተቀየሰው የገጠር ልማት በሀገሪቱ ሰፊ ቁጥር ያለውን አርብቶ አደር የዘነጋም ነበር። ኢህአዴግ በሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሳቤ መሰረት አርብቶ አደሩ ለማሕበራዊ መሰረትነት የማይመጥን አድርጎ እንደሚቆጥር ወይን በተሰኘው ድርጅታዊ መጽሔት እንደሚከተለው ተጠቅሶ ይገኛል።

> በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ መሬት ተከፋፍሎ የሚኖር አርሶ አደር አልነበረም። የህዝቡ የኑሮ መሰረት እንስሳትን በማራባትና በመከተል ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ ኑሮ የተመሰረተ ጠንካራ የነገድና የጎሳ ትስስር ያለው ነው። ይህ ነው የሚባል የመደብ ቅራኔ አልነበረም። መሰረታዊ የፖለቲካ ትስስርም በስጋ ወይም በደም ዝምድና የተመሰረተ ነው። በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የጐሳ መሪዎች ናቸው የሚያስተዳድሩት።

በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ከመስፍንነትና አርሶ አደር ቅራኔ በተለየ ጕሳዊ ትስስር የጎለበተ በመሆኑ ከዚያም አልፎ በገጠሩ ትርጉም ያለው የጠነከረ የመደብ ትግል ባለመኖሩ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል መሰረት የሚሆን መቆናጠጫ መደብ አልነበረም።

ከላይ በቀረበው ጽሑፍ አርብቶ አደሩ የሕብረተሰብ ክፍል የኑሮ መሰረቱ እንስሳት ማርባት በመሆኑና ይህ ነው የሚባል የመደብ ትግል ያልነበረው እና የጎሳዊ ትስስሩ ስለሚጎላ የኢህአዴግ ማሕበራዊ መሰረት ሊሆን አይችልም የሚል ሙግት ይዞ ቀርቧል። ይህ ሀሳብ በራሱ መሰረታዊ ተቃርኖ ያለው ስለመሆኑ በመጀመሪያ ኢህአዴግ በታዳጊ ክልሎች ውስጥ ያልተካለሉ አርብቶ አደሮችን እንደ ማሕበራዊ መሰረቱ መቁጠሩ ነው። ለምሳሌ፡- በኦሮሚያ ክልል ያለው የቦረና አርብቶ አደር ከሱማሌው እንደዚሁም ከከረዩ አርብቶ አደር ከአፋሩ አርብቶ አደር ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆንም የኦሮሚያው አርብቶ አደር ለማሕበራዊ መሰረትነት የሚመጥን የሱማሌው እና የአፋሩ አርብቶ አደር ደግሞ ለማሕበራዊ መሰረትነት የማይመጥኑ አድርጎ ይመለከታቸዋል። እንዲሁም በአማራ ክልል ያለው የአዊ ብሄረሰብ እና በቤንሻጉል- ጉሙዝ ክልል ያሉት የመተከል አካባቢ ብሄሮች፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ውስጥ ያሉ አርብቶ አደሮች ከጋምቤላ ክልል ሕዝብ ጋር መሰረታዊ ልዩነት የሌላቸውና በተመሳሳይ የአኗኗር ዘይቤ ያሉ መሆኑ ነው። በተጨማሪም አንድን ሕዝብ በአርብቶ አደርነቱ ብቻ ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ልዩነት ሲፈጠርበት እንደ አርሶ አደሩ ሁሉ የመደብ ጭቆና የሚደርስበት መሆኑን ፈጽሞ የዘነጋ ነው።

የኢህአዴግ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በታዳጊ ክልሎች ላይ የሚያራምደው አስተሳሰብ ሚዛን ያልጠበቀና የተዛነፈ መሆኑን ማረጋገጫው ዛሬም ያልተቀየረና ለማሕበራዊ መሰረትነት የማይበቁ ናቸው ብሎ በአቋሙ የፀና መሆኑ ነው። በመሆኑም በእነዚህ ታዳጊ ክልሎች ውስጥ የሚገኘው ንቃተ ህሊና ለኢኮኖሚ መሰረት የሆነው የእንስሳት ተዋፅኦ ምርት፣ የማዕድን ሀብት እና ሰፋፊ ለም መሬቶች ተገቢውን ትኩረት አግኝተው እንዳይለሙ ተደርጓል። በሌላ በኩል ጭቁን የከተማ ነዋሪ እና የገጠር አርሶ አደር የሆነው የሐረሪ ክልል ሕዝብን የወከለው ደርጅት የኢህአዴግ አባል ድርጅት ያልሆነበት መስፈርት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መርህ ወጣ ይላል የሚያስብል ነው።

ሌላው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ረገድ በማሕበራዊ መሰረትነት ያልተካተቱትና ለሀገሪቱ ዋነኛ የኢኮኖሚ ዋልታ ሊሆኑ የሚችሉትን የከተማ ልማት፣ የአገልግሎት ዘርፎች እና ኢንዱስትሪው ለበርካታ ዓመታት ትኩረት ተነፍጓቸው የቆዩ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ሀገራዊ ምርጫ ከተሞች የሥራ አጥነትና ማሕበራዊ ቀውስ ማዕከላት ወደ መሆን ደረጃ በመድረሳቸው የተቃዋሚዎች ብርቱ ፉክክር ማካሄጃ ሆኑ። ኢህአዴግ ከምርጫው ማግስት ያጋጠመውን ተግዳሮትና የሚታገልለትን ማሕበራዊ መሰረት ለመቃኘት አስገድዶታል። በዚህም ፓርቲው ይከተለው የነበረው የነጭ ካፒታሊዝም ርዕዮተ-ዓለም በመተው የልማታዊ መንግሥት እሳቤ ተከታይ መሆኑን ማስረዳት ጀመረ። ገጠርን ማዕከል ያደረገው የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራጂው ገሸሽ

በማድረግ ትኩረቱን የከተማ ልማት፣ ኢንዳስትሪ እና አገልግሎት ዘርፉ ላይ በማድረግ ለከተማው ሕዝብ ወገንተኛነት ያለው ድርጅት ለመሆን ጥረት ያደርግ ነበር።

ኢህአዴግ በየጊዜው በድርጅቱ ውስጥ በሚፈጠሩበት ውስጣዊ እና ውጫዊ ተፅዕኖዎች ምክንያት ሲከተል የነበረውን ርዕየተ-ዓለም ሲቀያይርና እታገልለታለሁ ሲለው የነበረውን ማሕበራዊ መሰረቱን እየለዋወጠ መምጣቱነ ለመገንዘብ ይቻላል። ይሁን እንጂ በተግባር ሲፈፀም የነበረው የዚህ ተቃርኖ ቢሆንም እስከአሁንም ድረስ ማሕበራዊ መሰረቴ የገጠሩ አርሶ አደር ነው በሚል የፖሊሲ የመከራከሪያ ያቀርባል። ከላይ የተጠቀሱትን የተቃርኖ ሀሳቦች በአስረጂ ነጥቦች ስንመለከት፡-

**1ኛ**/ የገጠሩን አርሶ አደር ለም የእርሻ መሬቶች በኢንቨስትመንት ስም ለግል ባለሀብቶች በመቸብቸብ በገጠር የሚኖሩ የአርሶ አደር ልጆችን መሬት አልባ እና ሥራ አጥ አደርጓል። እነዚህ ዘመናዊ የመሬት ከበርቴ ባለሀብቶች ከሀገሪቱ ባንክ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን በብድር መልክ የሚሰጣቸው ሲሆን ገንዘቡን ለታሰበለት ዓላማ ሲያውሉት አልታየም። በዚህም ልማት ባልተካሄደባቸው የእርሻ መሬቶች ምክንያት ውድ የመሬት ሀብትን ለግል ጥቅም በማባከን ገበሬውን መሬት አልባ ከማድረጉ ባሻገር በግብርናው ዘርፍ ላይ አሉታዊ ውጤት እያስከተለ ይገኛል። የዚህ ዋነኛ ተዋናይ የሆነውና የኢህአዴግ መስራች ድርጅት የነበረው ሕወሓት/TPLF ይህንን ትችት ሳይቀበለው ቆይቷል። ድርጅቱ በሚያሳትመው ልሳን ማለትም ወይን በተሰኘው መጽሔት *"በኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የተዋሃደ ፓርቲ ጥያቄ ለምን?"* በሚል ርዕስ ስር ተከታዩን ሀሳብ አስፍሮ ይገኛል።

> አሁን ለኢህአዴግ ማሕበራዊ መሰረት የሆነው አርሶ አደር የመሬት ጥያቄው የተመለሰበት፣ ሰላም ያገኘ፣ ይብዛም ይነስም ራሱን የሚያስተዳድርና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች የተመለሱለት፤ የድካሙ ውጤት ተጠቃሚ የሆነበት ነው። መሬት አልባ በነበረበት ወቅት መሬት ለማግኘት በራሱ ተነሳሽነት ህዝባዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ተጨባጭ አቅሙ ዝቅተኛ ነው። ዓበይት ጥያቄዎቹ የተመለሱለት ማሕበራዊ መሰረት ነው። ከተመለሱት ጥያቂዎች በማውጣት ወደ ከፍተኛ ተጠቃሚነት፣ አብዮታዊነትና ትራንስፎርሜሽን ሽግግር ለመሻገር የሚያነሳሳው ኃይል ያስፈልገዋል። በራሱ ተነሳሽነት ወደዚህ የሚገባበት ሂደት ዘገምተኛ ነው። በዚህ ረገድ የኢህአዴግ ድርሻ ታላቅና ልዩ ይሆናል። አርሶ አደሩ ወደ ሽግግር(ትራንስፎርሜሽን) ለመግባትና ላለመግባት የኢህአዴግ ድርሻ ልዩ ነው። አርሶ አደሩ ይብዛም ይነስም እምነቱን በኢህአዴግ ላይ ጥሎታል።[1]

ከላይ የቀረበውን ትንታኔ ስንመለከት አርሶ አደሩ ትልልቅ ጥያቄዎቹን በኢህአዴግ የተመለሰለት መሆኑንና ከነዚህም አንዱ መሬት አልባ የነበረው ገበሬ የመሬት ጥያቄው ሊመለስለት መቻሉን ይገልፃል። ይሁን እንጂ ይህ ሀሳብ በተግባር ሲፈተሽ የታሪክ መዛባት ያለበት የሃሰት ተረክ የሸፈነው ነው። መሬት አልባ የነበረው የሀገሪቱ ገበሬ የመሬት ጥያቄው የተመለሰለት በኢህአዴግ ሳይሆን በ1966ቱ አብዮት የመሬት ላራሹ አዋጅ መሆኑ

1 ወይን የሕወሓት የንድፈ ሃሳብ መፅሄት፤ ገጽ 14፤ መጋቢት 2011 ዓ.ም

የሚታወስ ሲሆን በዘመነ ኢህአዴግ ገበሬው ከእርሻ መሬቱ በመሠረተ ልማት ግንባታና በኢንቨስትመንት ሰበብ ተመጣጣኝ ካሳ ሳይከፈለው ሲፈናቀል የነበረና የዝናብ ደመና በጠፋ ቁጥር አንገቱን የሚደፋ ብሎም የምግብ ዋስትናውን ያላረጋገጠ መሆኑ ተጨባጭ ሀቅ ሆኖ እናገኘዋለን።

**2ኛ**/ ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት በልዩ ልዩ የአገልግሎት ዘርፎች እና በኢንዳስትሪው ላይ ለተሰማሩ ልማታዊ ለተሰኙ ባለሀብቶች ከቀረጥ ነጻና የብድር አቅርቦት የመሳሰሉትን ድጋፎች ሲያመቻች የነበረ ቢሆንም እነዚህ የማዳበሪያ ግብዓቶቸንና የማምረቻ መሣሪዎችን ጨምሮ ለአርሶ አደሩ የተፈቀዱ አልነበሩም። እስከዛሬም ድረስ ገበሬው መለስተኛ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ማምረቻዎችን እንኳ ተጠቃሚ መሆን አልቻለም።

**ሦስተኛ**/ በከተማ ለሚኖሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተጋረጠው የኑሮ ውድነትን ለመቅረፍ የታሰቡ የተለያዩ ድጎማዎችን መንግሥት ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም የዚህ ዓይት ድጋፎች በገጠሩ ነዋሪ ዘንድ የተለመዱ አይደሉም።

በመሆኑም ኢህአዴግ እና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍናው ያለማው የሕብረተሰብ ክፍል ማሕበራዊ መሰረቴ ነው የሚልለትን የገጠሩን አርሶ አደር ሳይሆን የፓርቲው ታማኝ አባላት እና ኪራይ ሰብሳቢ የግል ባለሀብቶች ደጋፊዎቹን ነው። ይህንን በተጨባጭ በሀገሪቱ የተመዘገቡ ልማቶችንና የኢኮኖሚ ዕድገቶችን በመመልከት በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል።

የኢህአዴግ መራሹ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋና የአስተሳሰብ ድክመት "ሊታገሉት የሚገባ መደባዊ ጠላት ወይም ተቀናቃኝ መፍጠር ካልተቻለ ሀገራዊ ልማት ማምጣት አይቻልም" ብሎ ድምዳሜ ላይ ተቸክሎ መቅረቱ ነው። በእርግጥ ይህ እሳቤ ኢህአዴግ የወለደው ሳይሆን የምስራቁ ዓለም የሶሻሊዝም ርዕዮተ-ዓለም አቀንቃኝ ሀገራት ለዘመናት ሲያራምዱት የነበረው ግራ ዘመም አስተሳሰብ ውጤት ነው። በሀገራችንም ከኢህአዴግ መመስረት አስቀድሞ እንደ መኢሶን፣ ኢህአፓ እና የመሳሰሉ ፓርቲዎች ተመሳሳይ ርዕዮተ-ዓለምና የመደብ ትግል በሚያካሂዱበት ወቅት በፊደልና በቃላት አጠቃቀም ልዩነት ሳይቀር እርስ በርስ እስከመጠፋፋት የደረሱበት የትግል ታሪክ አስመዝግበዋል።

ከላይ በተጠቀሱት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተፈጥሮአዊ ባህሪ እና በሀገሪቱ አሁን በሚስተዋለው የማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ መንስኤው ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ያልተጣጣመ አካሄድ መከተሉ ነው። በመሆኑም ሁለንተናዊ ብልጽግና፣ እውነተኛ ዴሞክራሲና ፌደራላዊ ሥርዓት ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ ሀገራዊ ማንነትን ከብሄር ማንነት በመለየት የቡድን መብትን ከግለሰብ መብት ጋር አጣጥሞ የሚሄድ አዲስ እሳቤ እንደሚያስፈልግ በግልጽ አመላካች ነው።

ከለውጡ ማግስት ብቅ ያለው አዲሱ የመደመር እሳቤ እንደፅንሰ ሀሳብ ሰብዓዊነትን ከሚመለከትባቸው እይታዎች እስከ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች በቀደሙ ጊዜያት ለሀገራዊ ግንባታ ለመሰረታዊ ችግሮች በመፍትሄነት የቀረቡ ናቸው። በተጨማሪም በአብዛኛው ከታላላቅ ዓለማቀፋዊ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ርዕዮተ-ዓለማት የሚቀዱ ፕሮግራሞችን በጠንካራና ደካማ ጎን ከፍሎ የሚቸት ሆኖ እሳቤው ለቁልፍ ችግሮች በመፍትሄነት የሚያቀርባቸው ስትራቴጂዎች ከርዕዮተ-ዓለም ተቸካይነት ፈቀቅ ያሉና

ተለዋዋጭነትን ማዕከል ያደረጉ ናው። ከሞላ ጎደል አማካኝ/መድሎት/ ሊባል የሚችል የፖሊሲ መስመር አማራጭን የሚከተል ይመስላል። ግቡም ሁለንተናዊ የሆነ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደሆነ ያብራራል። ሆኖም በተግበር የሚፈተሽበትን አግባብ ለማጤን ከአብታዊ ዴሞክራሲ ግትልትል ወይም ንብርብር አሻራ ራሱን ሙሉ ለሙሉ ስለማላቀቁ እርግጠኛ መሆን ያሻል።

## *መደምደሚያ*

በኢትዮጵያ ከነባሩ የፖለቲካ ባሕል እየተባለ የሚጠራው ሥርወ መንግሥት ዘመናዊ ሕገ መንግሥትን በሥራ ላይ በማዋል ወደ ከፊል ፊውዶ-ቡርዧ ሥርዓት መተግበር ጀመረ። በሥርዓቱ ኋላቀር ማሕበረ-ኢኮኖሚ ምክንያት ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ መሻሻያ ሳያደርግ ቀጠለ። በ1953ቱ የታህሳስ ግርግር የታየው ንቅናቄ ለጊዜው ጋብ ያለ ቢመስልም ሥርዓቱ ሕዝባዊ እቢተኝነትን እያስተናገደ መጣ። ቀጥሎም በ1966 ዓ.ም(እ.ኤ.አ1974 ዓ.ም) በሕዝባዊ አብዮት ለውጥ ተንኮታኮተ። አዲሱ የፖለቲካ ባሕል ማጠንጠኛውን የግራ ዘመም ማርክሲስት ሌኒኒስት መርህ ሆኖ ታወጀ።

ከዘውዳዊው ሥርዓት በኋላ ጎልቶ የታየው የመሬት ላራሹ እሳቤ እንደ ትግል ርዕዮተ-ዓለም ሰፊ ተቀባይነትን ያገኘ ነበር። በተለያየ ጊዜ ብቅ ብቅ ያሉት የለውጡ ሥርዓቶች ይከተሉት የነበረው ርዕዮተ-ዓለም ምንነትና ባሕሪያት ከነ ህፀፁ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባሕል ያመጣውን አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ በተገቢው መንገድ መፈተሽ ተገቢ ነው።

በዘመነ ደርግ የሶሻሊዝም መርህ በሥራ ላይ ሲውል ንዑስ ከበርቴን በማውገዝ መሬት ለአርሶ አደር ማከፋፈል የመሳሰሉ በጎ ጅምሮ ቢኖሩትም አምባገነናዊነትን በማጥበቁ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ አስነሳ። በተለይም ከምዕራቡና ምስራቁን ርዕዮተ-ዓለም ጎራ ፍትጊያ የሶቪየት ሕብረት መዳከም በሀገሪቱ የሰሜኑ ክፍል ረጅም ጊዜ የቆየው የትጥቅ ትግል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ አስከትሎ የደርግ መንግሥት ውድቀትን አፋጠነ።

ከደርግ ቀጥሎ ሥልጣን የተቆናጠጠው ኢህአዴግ ሀገሪቱን ለማስተዳደር በሥራ ላይ የዋለው የጎሳ ፌደራሊዝም ሀገሪቱን በዘጠኝ ክልሎች ከፋፈሎ ሃያ ሰባት ዓመታትን ዘለቀ። ኢህዴግ በአልባኒያ ሶሽያሊዝም አራማጅነት ማሕበራዊ መሰረቱን(legitimacy) ሰፊው አርሶ አደር መሆኑንና ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ መሆኑን ይፋ አደረገ። ይሁን እንጂ ደርግ ከሚያራምደው ሶሽያሊዝም እምብዛም የተለየ አልነበረም። ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የተሳከረ እሳቤው የሀገሪቱ ዋና ጠላት ድህነት ስለሆነ ቅድሚያ የምሰጠው ይህንኑ ነው በሚል ትርክት በአውራ ፓርቲነት ሌሎች የሰብዓዊና ዴሞክራሲዊ ጥያቄዎችን በመካድ ደፈጠጠ።

በኮሎኒያሊዝም ጭቆና ከነበሩት የአፍሪካ፣ የእስያና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች በአንጻሩ ኢትዮጵያ ነጻነት ያስገኘላትን ሥነ ልቦና ብታጣጥምም በተመሳሳይ ሁኔታ ከውጭ የርዕዮተ-ዓለም ጥገኝነት ራሷን ሙሉ ለሙሉ ማላቀቅ ተስኗት ቆይቷል። የኢህአዴግ አካሄድ ግልጸኝነት የጎደለው በመሆኑ በርካቶች በመከራከሪያነት አጀንዳዎችን ዛሬም ድረስ

ያነሳሉ። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማታዊ መንግሥትነት ጠባይ ተለውጫለሁ ቢልም በተግባር ግን በአጠራጣሪ የነጭ ካፒታሊዝም መዘፈቁ አልቀረም። ሆኖም ተደጋገሚ ምርጫዎችን ሲያፍን በቆየው ስልት መዝለቅ ያልቻለው ድርጅት መሰንጠቅ አጋጥሞታል። በ2010 ዓ.ም ውስጣዊ ተሃድሶ በሚመስል *"በቲም ለማ"* የሚመራ የኦሮሞ እና አማራ ጥምረት የለውጥ መንገድ ሊያሳካ ችሏል። በዚህም ዶ/ር ዐቢይ አህመድን ይዞ ብቅ ያለ ለውጥ መጠነኛ ማሻሻያዎችን በማድረግ ግን ከኢህአዴግ የወረሳቸውን ህፀፆች ይዞ አዲስ የመደመር ፍልስፍና እንደሚከተል አስታወቀ። ለውጡ ከዘውግ ፌደራሊዝም ሌላ መሰረታዊ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ሥር ነቀል ለውጥ ስለማድረጉ ግልጽ ባይሆንም በሀገራዊ አንድነት ላይ ብልጭታዎች ተስፋ ለሕዝቡ የሰጠ ይመስላል። ሆኖም ለውጡ መንታ መንገድ ላይ ቆመ ነው።

## ዋቢ ስራዎች


Aalen, Lovise (2002) "Ethnic Federalism in a Dominant Party State: The Ethiopian Experience 1991-2000" Report R 2002: 2 ChrMichelsen Institute Development Studies and Human Rights.

Aalen, Lovise (2006). "Ethnic Federalism and Self-Determination for Nationalities in a Semi-Authoritarian State: the Case of Ethiopia". *International Journal on Minority and Group Rights*. 13 (2): 243–261. *doi:10.1163/157181106777909849*

Aalen, Lovise (2006). "Ethnic Federalism and Self-Determination for Nationalities in a Semi-Authoritarian State: the Case of Ethiopia". *International Journal on Minority and Group Rights. 13* (2): 243–261. *doi:10.1163/157181106777909849*

Abbink, J. (1993). [Review of *A History of Modern Ethiopia, 1855-1974,* by B. Zewde]. *The Journal of Modern African Studies*, *31*(3), 521–523. http://www.jstor.org/stable/161218

Addis standard (2021-03-22). "News: Unknown number of people killed in ongoing violence in Oromia Special Zone and North Shewa Zone, Amhara region as warring factions trade blame". Addis Standard. Retrieved 2021-03-24

Addis Standard, 24 March 2021: Amhara & Oromia PP engage in war of words as relative peace returns to violence hit areas

Allo, Awol K. "How Abiy Ahmed's Ethiopia-first nationalism led to civil war". www.aljazeera.com. Retrieved 2021-01-20

Andreas Eshete (2003) 'Ethnic federalism: New Frontiers in Ethiopian Politics,' in first National Conference on Federalism, Conflict and Peace Building, Addis Ababa, United Printers PLC.

Borruso, P. (2013). Politics and Religion in Haile Selassie's Ethiopia: Apogee and Crisis of a Confessional African State (1916-1974). *International Journal of Ethiopian Studies*, 7(1 & 2), 101–124. https://www.jstor.org/stable/26586233

CAULK, R. A. (1972). Religion and the State in Nineteenth Century Ethiopia. *Journal of Ethiopian Studies*, *10*(1), 23–41. http://www.jstor.org/stable/41965842

Chanie, Paulos (2007). "Clientelism and Ethiopia's post-1991 decentralisation". *The Journal of Modern African Studies.* ***45*** *(3): 355–384. doi:10.1017/S0022278X07002662. S2CID 154750210.*

Crewett, W., & Korf, B. (2008). Ethiopia: Reforming Land Tenure. *Review of African Political Economy*, *35*(116), 203–220. http://www.jstor.org/stable/20406502

Crummey, D. (1990). Society, State and Nationality in the Recent Historiography of Ethiopia. *The Journal of African History*, *31*(1), 103–119. http://www.jstor.org/stable/182803

De waal A (August 20, 2018). "The Future of Ethiopia: Developmental State or Political Market Place." World Peace Foundation: Confflict Research Programme.

Desta, A. (2014). From Economic Dependency and stagnation to Democratic Developmental State: Essays on Socio-political and Economic Perspectives of Ethiopia. Trenton New Jersey: The Red Sea Press.

Desta, A. (2017). Rethinking Ethiopia's Ethnic Federalism." Germany: Lambert Academic Publishing.

Desta, A. (2012). "The Continuing Saga of Globalism: Comparing Ethiopia's Developmental State Strategies to those of Malaysia." International Journal of Management Sciences and Business Research. Vol. 1, Issue, 11, pp. 87-103.

Embassy of Ethiopia, London. (2020). "Context and Updates on Current Issues in Ethiopia". Embassy of Ethiopia, London. 2020-07-08. Retrieved 2020-12-16

EPRDF (2013) የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ 2005 ዓ.ም (ገፅ 25-26)/*Ya Serawit Genbata Ba Abiyotawi Democracy* 2011, pp.25-26

EPRDF. (2005). "Building an Army in Revolutionary Democracy

Ethiopian News Agency, 29 December 2020. Tigray Prosperity Party Inaugurates Office in Mekelle.

EZEGA. (2019). "The EPRDF Officially Ends; The Prosperity Party Begins". Ezega News. 2019-12-26. Archived from the original on 2020-12-16. Retrieved 2020-12-16.

EzEGA. (2020). "The EPRDF Officially Ends; The Prosperity Party Begins". Ezega News. 2019-12-26. Archived from the original on 2020-12-16. Retrieved 2020-12-16.

Ezega. (2020). "Who Will Win the Next Ethiopian Elections?" January 10, 2020 – via www.ezega.com

Gebeyehu, T. (2010). The Genesis and Evolution of The Ethiopian Revolution and The Derg: A Note on Publications by Participant in Events. History in Africa, 37, 321–327. http://www.jstor.org/stable/40864628

Gebeyehu, T. (2010). The Genesis and Evolution of The Ethiopian Revolution and The Derg: A Note on Publications by Participant in Events. *History in Africa*, 37, 321–327. http://www.jstor.org/stable/40864628

Gebreluel, Goitom. "Analysis | Ethiopia's prime minister wants to change the ruling coalition. Who's getting left out?". Washington Post. ISSN 0190-8286. Retrieved 2021-01-24

Gedamu, Yohannes (13 December 2019). "The new political party of Ethiopia's Abiy holds much promise but faces significant hurdles". Quartz Africa. Quartz. Retrieved 5 January 2020.

Gedamu, Yohannes. "The new political party of Ethiopia's Abiy holds much promise but faces significant hurdles". *Quartz Africa.* Retrieved 2021-01-20.

Gedamu, Yohannes. "The new political party of Ethiopia's Abiy holds much promise but faces significant hurdles". Quartz Africa. Retrieved 2021-01-20.

Gedamu, Yohannes. "Why Abiy Ahmed's Prosperity Party is good news for Ethiopia". www.aljazeera.com.

Gelan, A. (29 October, 2018). "Ethiopia: What is Happening to EPRDF's Developmental State? Addis Standard (Addis Ababa). Available at http://allafrica.com/stories/20181031340.html.

Gerth-Niculescu, Maria. "Can PM Abiy Ahmed breach Ethiopia's ethnic divide?". Deutsche Welle.

Habtewold, Melaku (December 24, 2019). "Why Prosperity Party is needed"- via www.ethiopia-insight.com.

Harbeson, J. W. (1977). Perspectives on the Ethiopian Revolution. *Ethiopianist Notes*, *1*(1), 1–8. http://www.jstor.org/stable/42731357

Jan Nyssen, 2021. The situation in Tigray at the beginning of 2021. Preprint for HBS.

Kebede, M. (2015). The Ethiopian Student Movement: A Rejoinder to Bahru Zewde's <em>The Quest for Socialist Utopia</em>. *Northeast African Studies*, *15*(1), 175–186. https://doi.org/10.14321/nortafristud.15.1.0175

Lemma, L. (1979). The Ethiopian Student Movement 1960-1974: A Challenge to the Monarchy and Imperialism in Ethiopia. *Northeast African Studies*, 1(2), 31–46. http://www.jstor.org/stable/43660011

Lewis, I. M., & Jewell, P. A. (1976). The Peoples and Cultures of Ethiopia [and Discussion]. *Proceedings of the Royal Society of London. Series B, Biological Sciences*, 194(1114), 7–16. http://www.jstor.org/stable/77087

Lipset, S. M. (1994). The Social Requisites of Democracy Revisited: 1993 Presidential Address. *American Sociological Review*, 59(1), 1–22. https://doi.org/10.2307/2096130

Mamdani, Mahmood (2019-01-03). "Opinion/The Trouble with Ethiopia's Ethnic Federalism (Published 2019)". The New York Times. ISSN 0362-4331. Retrieved 2021-01-24

Markakis, J. (1989). Nationalities and the State in Ethiopia. *Third World Quarterly*, *11*(4), 118–130. http://www.jstor.org/stable/3992334

MEIG programme. (2021). The Fallout of Ethnic Federalism". MEIG Programme. MEIG programme 12 May 2021. Retrieved 30 July 2021

Melakedingel, Nolawi (10 May 2013). "The Oddities of 'Revolutionary Democracy'". Addis Standard. Retrieved 1 July 2014.

New Business Ethiopia, 19 February 2020: Abiy meets Prosperity Party leaders from Tigray.

Pankhurst, R. (1997). Ethiopian Dynastic Marriage and the Béta Esra'él (or Falashas). *Africa: Rivista Trimestrale Di Studi e Documentazione Dell'Istituto Italiano per l'Africa e l'Oriente*, *52*(3), 445–454. http://www.jstor.org/stable/40761157

Proseperty Party. (2020a). ብልጽግና ፓርቲ (2020). የፖለቲካ ብልጽግናን የማረጋገጥ ትልም እና ፈተናዎች፤ (ያልታተመ)።

Proseperty Party. (2020b).ብልጽግና ፓርቲ (2020). *ሀገራዊ የለውጥ እርምጃዎች የለውጡ ምንነት፣ ስኬቶች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና መሻገሪያ ስልቶች፤ (ያልታተመ)።*

Proseperty Party. (2020c). ብልጽግና ፓርቲ (2020). ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ትልም እና ፈተናዎቹ፤ (ያልታተመ)።

Shumuye, M. (2017). The Role of the Developmental State in Northern Ethiopia፡ Raya Valley Ground water Irrigation Project: An Institutional Economics Perspective. Unpublished Doctoral dissertation, Stellenbosch University, South Africa.

Tareke, G. (2002). [Review of *A History of Modern Ethiopia 1855-1991; From Guerrillas to Government: The Eritrean People's Liberation Front*, by B. Zewde & D. Pool]. *The International Journal of African Historical Studies*, *35*(2/3), 587–590. https://doi.org/10.2307/3097685

Vaughan, Sarah (2003). "Ethnicity and Power in Ethiopia" (PDF). Archived 13 August 2011 at the Wayback Machine University of Edinburgh: Ph.D. Thesis. p. 168.

Yibeltal, Kalkidan. "Ethiopia's Abiy Ahmed gets a new ruling party". BBC

ብልጽግና ፓርቲ (2020). *ሀገራዊ የለውጥ እርምጃዎች የለውጡ ምንነት፣ ስኬቶች፣ ቀጣይ ፈተናዎችና መሻገሪያ ስልቶች፤ (ያልታተመ)*

ብልጽግና ፓርቲ (2020). ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ትልም እና ፈተናዎቹ፤ (ያልታተመ)

ብልጽግና ፓርቲ (2020). የፖለቲካ ብልጽግናን የማረጋገጥ ትልም እና ፈተናዎች፤ (ያልታተመ)

ብልጽግና ፓርቲ (2021). Prosperity's view on ideology. ብልጽግና ስለ ርዕዮተ-ዓለም ምን ይላል? https://www.youtube.com/watch?v=TWR9X-CA6T0

ብልጽግና ፓርቲ (2021). ብልጽግና እና ማህበራ ዊዘርፍ https://www.youtube.com/watch?v=ezc1Yf0EtvQ

ብልጽግና ፓርቲ (2021). ብልጽግና እና ኢህአዴግ ምንና ምን ናቸው? https://www. youtube.com/watch?v=mCcyH-Klp7A

ብልጽግና ፓርቲ (2021). ብልጽግና እና ኢኮኖሚ https://www.youtube.com/watch?v=vUcy1iTu0Gc

ብልጽግና ፓርቲ (2021). ብልጽግና እና የብዝሃነት አያያዝ https://www.youtube.com/watch?v=djb5nQXR-KQ

ብልጽግና ፓርቲ (2021). የብልጽግና ማኒፌስቶ (ያልታተመ)፤ https://prosperity.org.et/?page_id=3609&lang=am

ብልጽግና ፓርቲ (2021). የብልጽግና አጀንዳዎች https://www.youtube.com/watch?v=Wt1PAW6wfvM

ብልጽግና ፓርቲ (2021). የብልጽግና ፓርቲ ፕሮግራም፤(ያልታተመ) prosperity.org.et/wp-content/uploads/2021/pdf

ብልጽግና ፓርቲ (2021). ዴሞክራሲና የብልጽግና እይታ https://www.youtube.com/watch?v=cZ3wY_2wk1M

ወይን የህወሓት ንድፈሃሳብ መፅሄት፤ ገጽ 20፤ መጋቢት 2011 ዓ.ም

የሠራዊት ግንባታ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ 2005 ዓ.ም (ገፅ 25-26)

*Abebe Zegeye*
*Co-Director, Cradle: Center for Research and Development in Learning*
*Addis Ababa, Ethiopia*

*&*

*Ayele Addis Ambelu*
*Assistant Professor in Media and Communications*
*Injebara University*